

# ሐዲስ

19ኛ ዓመት ቁጥር 64

ታህሳስ ወር 2017 ዓ.ም



"በመፍጠርና በመፍጠን ፕሮጀክትን በውጤታማነት በመምራት ተቋማዊ ባህልን በማፅናት በመንገድ ዘርፉ የኢትዮጵያን የመነሳት ዘመን እውን እናደርጋለን "

አብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

## ራዕይ

በመረጃ የበለፀገ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ በ2022 እውን ሆኖ ማየት

## Vision

To see a society with rich information and all rounded active participation for a better understanding on fundamental regional and country level affairs for having common consensus in 2030

## ተልዕኮ

በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ መሪ ሚና በመጫወት በህብረተሰቡ መካከል ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በመሰረታዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዙሪያ የመላውን ህዝብ ግንዛቤ በማዳበር ሁለንተናዊ እድገታችንን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ለራዕያችን ስኬታማነት የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ፣

## Mission

playing a leading role in government communication information for a successful information exchange with in a society. to enhance the awareness of the people on the fundamental government policies strategies. plans and programs for a better step of succession our vision by stron collaboration.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በየ 3 ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

የታሕሳስ ወር 2017 ዓ.ም

19ኛ ዓመት ቁጥር 64

# ሐዲስ

**አዘጋጆች**

- ፍሬው ምናለ
- ይበልጣል መኮነን
- ሲሳይ ጌቴ
- ደፋሩ እምሬ

**አርታኢ**

- ጋርዳቸው አንሙት
- ፈቃዱ ገድፍ አስናቀ

**ህትመት ስርጭትና ክትትል**

- ደባሱ ካሣ

**ግራፊክስ ዲዛይን**

- ጌታሁን ላቀ

ገጽ

መልዕክቶች፡-

ደብዳቤዎች፡-

ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር፡-

የፍልሚያዉ ባህር . . . ........................................ 9

ልማት/ኢኮኖሚ፡-

ሸማ በየፈርጁ ........................................ 13

ባህል/ ታሪክ፡-


ሰልፍና መድፍ ........................................ 17

ማህበራዊ፡-

የክፍያ ጭማሪና የወላጆች ስሜት ........................ 22

ልዩ ልዩ

ከእረኝነት ባሻገር........................ 27




ውድ  አንባቢያን መጽሔታችንን በማንበብ  አስተያየታችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተሉት አድራሻዎቻችን ይላኩልን


Facebook- Amhara Communications

ኢሜል- anrsnproduction@ gmail. com

ዩቲዩብ- Amhara Communications

ቲውተር- @ANRSGCAO

ዌብሳይት- www.amharacomm.gov.et

ስልክ- 058 220 09 40 ፤ 058 226 5921፣ 058 220 4107

ፋክስ- 058 220 1105 / 058 226 4172

ፖ.ሣ.ቁ 607


የዝግጅት ክፍሉ



ያሰለፍነው  በጀት ዓመት ሶስት አቅሞችን ማለትም የመንግስት፤የህዝብና የድርጅት አቅሞችን በመጠቀም በ2016 በጀት የያዝናቸውን የመንገድና ተያያዥ መሰረተ ልማት ስራዎችን በውጤታማነት በመፈፀም ከተቋሙ ባሻገር በክልል ደረጃ ፕሮጀክቶችን በጥራት በማቀድና በውጤታማነት መምራት የሚያስችል  አቅም ተፈጥሯል፡፡ የተፈጠረውን አቅም የበለጠ ማጠናከር የሚያስችል ከመሆኑ ባለፈ  የሕዝባችንን የተጠራቀመ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚነት ጥያቄን  መገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሌት ተቀን በመስራት ፕሮጀክቶችን በጊዜና በጥራት መፈፀም አለብን የሚል አመለካከትና ቁርጠኝነት ተፈጥሯል፡፡ ይህ ደግሞ የሁሉም ነገር መሰረት በመሆኑ ፕሮጀክቶችን በውጤታማነት የመምራትና ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ ለዘርፉ ብዙ ምላሽ የሚሰጥ ቀዳሚ ጉዳይ ነው፡፡

በክልላችን በገጠርም ሆነ በከተማ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ዘላቂነትን በማስቀጠል፣ ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶች በሁሉም አካባቢዎች በስፋትና በጥራት ባለፉት ዓመታት ሲሰራ ቆይቷል።

በመሆኑም በ2017 በጀት ዓመት ዕቅድን በውጤታማነት ማሳካት ሁለት መሰረታዊ ግቦችን እናሳካለን፡፡ የመጀመሪያው በምርጫ መንግስት ስንሆን ባለፉት አራት ዓመታት ያልፈፀምናቸውን ግን ደግሞ ቃል የገባንባችውን ተግባራት  አሟጠን የበጀት ዓመት ዕቅድ አካል አድረገን የምንፈፅምበት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በ25 ዓመታት በተያዘው የቁጭት ዓመት ምቹ መደላድል የምንፈጥርበት ዓመት ነው፡፡

መንግስት ከመቸውም ጊዜ በላይ የጋራ ገዥ ትርክት በ2018፤በ2023 እና በ2040 በማስቀመጥ የሥራ ባህልና የምርታማነትን መጠን መቀየር የሚያስችል የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ እንገኛለን፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ግለቱን ጠብቆ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የመንገድ መሰረተ ልማት አይተኬ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህንን ታሪካዊ ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት የላቀ ነው፡፡

ስለሆነም በክላላችን ፕሮጀክት በውጤታማነት የመምራት ተቋማዊ ባህል መሰረት የምናፀናበትና በመፍጠርና በመፍጠን ፕሮጀክትን በውጤታማነት በመምራት ተቋማዊ ባህልን በማፅናት በመንገድ ዘርፉ የኢትዮጵያን የመነሳት ዘመን እውን እናደርጋለን ፡፡ ለዚህም ደግሞ የቢሯችን መዋቅር  ልዩ ልዩ አጋር እና ባለድርሻ  አካት የጀመርነውን የስራ ባህል ለውጥ በማጠናከር የሁሉም ነገር መፍቻ ቁልፍና የህዝብ ጥያቄ የሆነውን የመንገድና ተያያዥ መሰረተ ልማት ስራዎችን በውጤታማነት በመምራት በማጠናቀቅ ሪቫን የምንቆርጥበት ዓመት  ብቻ ሳይሆን ለዘርፍ ከሚመደበው ሀብት በተጨማሪ አማራጮችን በማስፋት ሀብት የምንፈጥርበት  ዓመት ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ሦስቱን የመንግስት አቅሞች በተሟላ መንገድ፤ በመፍጠርና በመፍጠን መጠቀም የሚያስችል ዘመኑን የዋጀ ተቋም ግንባታ ተቀደሚ ተግባር በመሆኑ አጠናክረን ቀጥለናል፡፡

ጋሻዉ አወቀ ትኩዬ(ዶ/ር)

**የአብክመ መንገድ ቢሮ ኃላፊ**



የአብክመ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ በቢሮ ደረጃ በተቋቋመ ማግስት መጋቢት 7 2017 ዓም በይፋ ያስመረቅነውና ያስተዋወቅነው ሎጎ በምስል ከታች የሚታየው ሲሆን፤ የሎጎው ጥቅልና ዝርዝር ትርጓሜው የቢሮውን የወደፊት ጉዞንና ክልላዊ ተጠባቂ ሃላፊነትን በሚገልጽ መልኩ የተዘጋጀ ነው። ጠንካራ፣ አይበገሬና ነገን የሚሻገር ተቋማዊ ባህልና ጥንካሬን በመገንባት የሚከተሉት ቁልፍ የትኩረት መስኮች ላይ መሬት ላይ የወረደ ስራ እየሰራን ነው።

አስተማማኝ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት መገንባት ለዲጂታላይዜሽንና ለዝመና አስቻይ የሆነ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት መገንባት ተቀዳሚ ተግባር ሲሆን፤ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶችንና የመስመር ዝርጋታዎችን እንዲሁም የመረጃ ማቆሪያ ቋቶችንና ማዕከላቶችን የያዘ ቁልፍ ዘርፍ ነው። ዲጅታል ኢኮኖሚውን ለማሳለጥ የሚያስችል ደረጃቸውን የጠበቁ የኢንኩቤሽን እና የአክስለሬሽን ማዕከላትን፣ የኢኖቬሽን ሃቦችን፣ የመሞከሪያ እና የመፈተሻ ቤተ-ሙከራዎችን እንዲሁም የቴክኖሎጂ ፓርኮችንና የመሳሰሉትን መሠረተ-ልማቶች ደረጃቸውን የማሻሻል፤ እንደ አዲስ የመገንባትና የማስፋፋት ስራን እንሰራለን።

የሰው ሃይል አቅም ግንባታ በፈጣን የልውጠት ማዕቀፍ ውስጥ እየተጓዘ ያለውን የቴክኖሎጂ ምህዳር ውስብስብነትን ታሳቢ ያደረገ የሰው ሃይል አቅም ግንባታ ስራ ይሰራል። በሁሉም የማህበረሰብ ክፍልና የመንግስት መዋቅር ላይ ፈጣኑን የቴክኖሎጂ ምህዳር ልውጠት ሂደትንና አዝማሚያን የሚመጥን ዲጂታል ግንዛቤ እንዲኖር በማድረግ ለዝመናው ዘርፍ መደላድልና አስቻይ የሆነ ሁነትን የመፍጠር ስራ በሰፊው እናከናውናለን።

የሲስተም ልማትና አውቶሜሽን ክልላዊ የመንግስት መዋቅራዊ አደረጃጀትን፣ የተቋማት የስራ ስምሪትና ኃላፊትን እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ የሂደት ቅድም-ተከተሎችን መሰረት ያደረገ የሲስተም ልማትና አውቶሜሽን ስራ እንሰራለን። የምንሰጣቸውን አገልግሎቶችንና የምናመርታቸውን ውጤቶች እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብትና ቅርሶቻችንን በተገቢው አድማስ ልክ ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ፤ የመንግስት አስተዳደራዊ ወጪንና የተገልጋይን ድካም የሚቀንሱ፣ የሃብትና የጥረት ድግግሞሽን የሚያስቀሩ፣ የስራንና የአፈጻጸምን ሂደት በግልጽ ማሳየት የሚያስችሉ ሲስተም ልማቶች እያከናወን እንገኛለን።

የቴክኖሎጂ ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት በሁሉም የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ዘርፍ ላይ መነሻና መቆጣጠሪያ ስርዓቶችን የማዘጋጀትና የመቆጣጠር ስራ እንሰራለን። የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶችን፣ ሲስተሞችን፣ የሰው ሃይል አቅሞችናን የፈጠራ ሃሳቦችን ከጥራት፣ ከተናባቢነት፣ ከአካባቢ ጥበቃና ከተሻጋሪነት አንጻር ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችሉ ስርዓቶች ተዘጋጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል።

ፈጠራን ማህበረሰባዊ ባህል ማድረግ ሀገር በቀልና ከሌላ ቦታ የሚቀዱ ወይም የሚዳቀሉ እውቀቶች ሳይሳዊ ሂደትን ተከትለው ችግር ፈቺ ፈጠራ የሚሆኑበት ምቹ መደላድልን እንፈጥራለን። እነዚህ ፈጠራዎችና እውቀቶች ከለጋነት ደረጃቸው ጀምሮ እስከ ጉልምስናቸውና የቴክኖሎጂ ሽግግር እስከሚፈጠር ድረስ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እናደርጋለን። የፈጠራ ሃሳቦች ወደ ገንዘብና ንብረት የሚቀየሩበት ምቹ መዳለድል እንዲፈጠር የሚያስችሉ ስርዓቶች እንዲዘጋጁ የሚያስችሉ ስራዎችና ትብብሮች እየተከናወኑ ነው።

የአብክመ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ የተዋረድና የጎንዮሽ መዋቅርና አደረጃጀት ከፌደራል እስከ ክልል ተቋማት ድረስ የተሳለጠና የተሰናሰነ ትስስር እንዲኖረው ተደርጎ እየተሰራ ሲሆን፤ የቢሮው ተቋማዊ ባህልና ቁመና እንዲሁም የሰው ሃይሉ ቅድመ-ዝግጅት አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የሚጠበቀውን ክልላዊ አበርክቶውን እውን ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ይገነባል።

አቶ አቤል ፈለቀ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ ኃላፊ




የአብክመ የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን  በሳይንሳዊ እውቀት ላይ ተመስርቶ በክልሉ አካባቢን የሚጎዱና የሚበክሉ ተግባራትን በመከታተል፣ በመመርመር፣ በመቆጣጠርና የብዝሃ ህይዎት ሃብቶች መመናመንን በመከላከል የቀጣዩን ትውልድ የመወሠንና የመጠቀም መብት ሣይጋፋ በዘመኑ ላለው ትውልድ የተሻለ ጥቅም መስጠት የሚያስችል ዘላቂና ህጋዊ የአካባቢ፣ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ሥርዓትን ማስፈንን ተልእኮው በማድረግ የአካባቢ ጥበቃ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ፣ የደንና የዱር እንስሳት ሃብትን በአግባቡ ለመጠበቅና ለማልማት ብሎም በእነዚህ ተግባራት ቅኝት  በ2022 ለሰውና ለዱር እንስሳት መኖሪያ ምቹ የሆነ አካባቢ እንዲፈጠር ለመስራት የተቋቋመ ተቋም ነው።

ባለስልጣኑ ቀደም ሲል በአዋጅ 232/2008 ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ 28 የሚደርሱ ዋና ዋና ተግባራትን መሠረት በማድረግ በአካባቢ፣ ደን እና ዱር እንስሳት  ጥበቃና ልማት ዘርፍ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ቆይቷል፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል መንግስት የተቋሙን ተግባርና ኃላፊነት ማሻሻልና ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን በተቋማት መልሶ ማደራጀት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 280/2014 መሰረት የተሰጠውን 39 ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ዘርፈ ብዙ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ስለሆነም በክልሉም ሆነ በፌደራሉ መንግስት የተደነገጉ የአካባቢ ጥበቃና ደህንነት ህጎችን እና በሀገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ ውስጥ የሰፈሩ መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን በማስተባበር፣ በመንግስትም ሆነ በግል ኘሮጀክቶች (በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ ሕጎችና መርሃ - ግብሮች) ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማና የአካባቢ ክዋኔ ኦዲት ተግባራትን በማከናወን፣ ልዩ ልዩ የአካባቢ ህጎችንና መመሪያዎችን በማውጣት፣ የአካባቢ ህጎች እንዲከበሩና ከብክለት ነጻ የሆነ ለመኖሪያ ምቹና ጤናማ አካባቢን ለመፍጠር ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡  ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚደረገውንና እንደ ሀገር የተደረገውን አለማቀፋዊ ስምምነትም በክልላችን ተግባራዊ ለማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ በሆኑ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች የተፅዕኖዎች ማቃለያ እና መቋቋሚያ ስልቶች እንዲያከናውኑና እነዚህ ተግባሪ ተቋማት ይህንን ዘርፍ በመደበኛ እቅዳቸው አካተው በመተግባር የሚቀንሱትን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ታሳቢ የሆነ ተግባር እንዲያከናውኑ በክትትልና ድጋፍ የማስተባበር እና የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግስትም ሆነ ለህዝብ እንዲደርስና የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡ ለማድረግ የተጀማመሩ ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡



በላብራቶሪ የታገዙ የአካባቢ ምርመራ ስራዎች

የተፈጥሮ ደኖችን፣ የብዝሃ ህይወት ሀብቶች መገኛ የሆኑ ብሔራዊ ፓርኮችና የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራዎችን በመጠበቅና በማልማት የአሁኑንና የመጭውን ትውልድ የመጠቀም መብት በማይጋፋ ሁኔታ በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውሉና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖ*ሚን ከመገንባት ባሻገር የቱሪዝም ኢኮኖሚውን ለመገንባት ጉልህ ድርሻ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡

በክልላችን የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖችን በመንግስትና በህብረተሰቡ ቅንጅት እንዲጠበቁና እንዲለሙ በማድረግ፣ የተራቆቱ ተራራማ ቦታዎችን ከልሎ በማልማት፣ ከደን ሀብት ውጤቶች የሚሰበሰበውን የሮያሊቲ ክፍያ አፈፃፀም እንዲያድግ እና በዘርፉ ለክልሉ ወጣቶችና ሴቶች የሚፈጠረው የስራ እድል ፈጠራ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ እንዲሆን በየደረጃው ከሚገኘው መዋቅራችን፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የተቀናጀ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ነገር ግን ከእነዚህ  ውጤቶች ጎን ለጎን የሰው  ልጅ ለህልውናው መሰረት የሆኑትን ህይወታዊና ህይወታዊ ያልሆኑ ቁሶችን የሚያገኝበትን አካባቢውን በቁጠባና በአግባቡ ባለመጠቀሙ እንዲሁም በምርት ሂደት የሚፈጠሩ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በአግባቡ ማስወገድ ባለመቻሉ ምክንያት በርካታ ችግሮች እየተከሰቱ፣ የተፈጥሮ ደኖች፣ ጥብቅ ስፍራዎችና ብሔራዊ ፓርኮች  በህገ ወጦች ድንበራቸው እየተጣሰ ዛፎች እየተቆረጡ የዱር እንስሳት እየተሳደዱና ከፍተኛ ውድመት እየደረሰባቸው መሆኑ የጥበቃና ልማት ተግባሩን እየተፈታተነ ያለ ተግዳሮት ሆኗል፡፡

ችግሮቹ ከቀጠሉ ደግሞ የሰውን ልጅ በንጹህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብትን ጨምሮ በዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ ፈተና በመሆናቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት በየደረጃው ከሚገኘው የአካባቢ እና ደን ጥበቃ መዋቅራችን ጋር በአካባቢ ጥበቃ ተግባራት የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች ላይ በቅንጅት በመስራት እና የህዝብን ጥቅምና ደህንነት ወደ ጎን ትተው አካባቢን በሚበክሉና የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ተቋማት ላይ አስተማሪ የሆነ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድ በጋራ መረባረብ ይገባል፡፡

በመጨረሻም አካባቢን መጠበቅና ማልማት የሁሉንም አካላት ቅንጅታዊ እርብርብ የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን በመረዳት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት የምትገኙ የአካባቢ ጥበቃ ተቆርቋሪዎችን ጨምሮ መላው የክልላችንን የህብረተሰብ ክፍል፣ የሚመለከታችሁ የአስተዳደርና የህግ አካላት እንዲሁም በየደረጃው የምትገኙ የባለስልጣኑ አመራሮችና ባለሙያዎች የባለስልጣን መ/ቤታችንን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ያደረጉ ተግባራትን በማከናወን የሚጠበቅብንን ሚና እንድንወጣና ለቀጣዩ ትውልድ ምቹና ጤናማ አካባቢን ለመፍጠር እንድንሰራ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተስፋሁን አለምነህ ይስማው

የባለስልጣኑ ኃላፊ

# የፍልሚያው ባህር

**በሲሳይ ጌቴ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እየታዩ ያሉት ፉክክሮች ጤናማ አይደሉም፡፡ አንድም ለቀጣናችን ብሎም ለአፍሪካችን ተስፋን የሰነቁ ሳይሆኑ በርሃብ ላይ ርሃብን በጦርነት ላይ ጦርነትን በችግር ላይ ችግርን የሚያክሉ እየሆኑ ነው።

ቀደም ሲል በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ደም አፋሳሽ ጦርነት ተፈጥሮ ነበር፡፡ በሱማሊያ ውስጥ የአልሸባብን እንቅሰቃሴ ተከትሎ በቀጣናው እስካሁን ድረስ ግጭቱ አልጠፋም፡፡ በጅቡቲና ኤርትራ፣ በኤርትራ እና በየመን መካከል በሐኒሽ ደሴት ዙሪያ ተከስቶ የነበረው ግጭት፣ በኢትዮጵያ እና ሱዳን መካከል ያለው ዉጥረት ሁሉ የውጭ ጣልቃ ገብነት አለበት፡፡

አሁን አሁን ደግሞ በቀይ ባህር በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኙና የራሳቸው የባህር በር ያላቸዉ የገልፍ ሃገራት ሳይቀር በቀይ ባህር አካባቢ የሚያሳዩት ፉክክርና አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶች “እውን የቀጣናቸዉንና የቀጣናችንን ሰላምና መረጋጋት ለማምጣት ታስቦ ነው? ወይስ የሶስተኛ ወገን አጀንዳ ይዘው መጥተው ለማስፈጸም ነው?” ብለን እንድንጠይቅ ያደርጋል። የቀጣናውን እንቅስቃሴ በአንክሮ ለሚከታተል ሰው በእርግጥም እነ ሳዉዲ አረቢያ፣ የተባበሩት አረብ ኢመሬት እና ቱርክን ጨምሮ በቀይ ባህር አካባቢ የየራሳቸዉን ጦር ሰፈር ገንብተዋል፡፡

በእርግጥ ከቀይ ባህር ሃገራት በተለይም ከአፍሪካ ቀንድ ሃገራት መካከል ጅቡቲን ብንወስድ ሃያላን ሃገራት የጦር ሰፈር ገንብተዉ ከፍተኛ ፉክክር የሚያደርጉባት ሃገር መሆን ከጀመረች ሰነባብታለች። ቻይና ፣ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ጃፓን እና አሜሪካ በጅቡቲ የየራሳቸውን የጦር ሰፈሮች ገንብተው የአፍሪካን የተፈጥሮ ሐብት በኢንቨስትመንት ስም ወይም የየራሳቸዉን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚል ሽፋን ጤናማ ያልሆነውን ፉክክራቸዉን በማጧጧፍ ላይ ናቸው።



እምቢአለ

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና አለም አቀፍ ጥናት መምህር

ለበርካታ ሺህ ዓመታት የራሷ የባህር በር ያላት ኢትዮጵያ ከ30 ዓመታት ወዲህ የወጭና የገቢ ንግድ የምታሳልጥበት የራሷ የሆነ ወደብ የላትም፡፡ እንደ ወርልዶሜትር መረጃ እ.ኤ.አ 2025 በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከ134 ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህም በዓለም የባሕር በር ከሌላቸው ሃገራት ከፍተኛ የህዘብ ብዛት ያላት ሃገር ያደርጋታል።

የባህር በር ያጣችበትን፣ የባህር በር በምን መንገድ መጠቀም እንደመትችል፣ የሃያላኑ ሃገራት ፉክክር በአፍሪካ ቀንድ ሃገራት ላይ ምን ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችልና እየገነቡት ያለው የጦር ሰፈር አንድምታውን በተመለከተ የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ጥናት መምህር ከሆኑት ከመምህር እምቢአለ በየነ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

የአንድን ሃገር የሃይል ሚዛን፣ አሰላለፍና አቅምን ለመለካትና ለማሻሻል የባህር በር ወሳኝ ነው፡፡ ሰፊ የሆነ የህዝብ ቁጥርና የቆዳ ስፋት ቢኖርም ያለ ባህር በር የኢኮኖሚ እድገት፣ የፖለቲካ ደህንነትና ሉዓላዊነትን ማስጠበቅ አይቻልም፡፡ ኢትዮጵያ ያላትን ሃይልና አቅም ለማሳነስ የሚፈልጉ ሃይሎች ከቀይ ባህር ለመነጠል በርካታ ስራዎችን ሰርተዋል፡፡ ሆኖም ግን ከቀጠናውም ላለመለየት ከፍተኛ የሆነ ትግል ስታደርግ የቆየች ብትሆንም በመጨረሻ የባህር በር የሌላት ሃገር ሆናለች፡፡ የአረብ ሃገራትና ምዕራባዊያን “ቀይ ባህር የአረብ ሃገራት ንብረት ብቻ ነው” የሚል ፍልስፍና ስለነበራቸው በሚገባ ታቅዶና ተጠንቶ ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ማራቅ ችለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር በመገለሏ ምክንያት በኢኮኖሚና በፖለቲካዊ ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ የአሰብና የምጽዋ ወደብ መጠቀም ከአቆመች በኋላ በዋናነት እየተጠቀመች ያለችው የጅቡቲን ወደብ ነው፡፡ በየ ዓመቱም ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ እያወጣች ለወደብ ኪራይ ትከፍላለች፡፡ ከኪራይ መክፈል ባለፈ ወደ ሃገር ቤት ለመግባት በመዘግየቱ ምክንያት ተጨማሪ ወጭ እና የዋጋ ግሽፈት በማባባስ የምጣኔ ሃብት እድገት እንዳይኖር አድርጓል፡፡ በፈለገችው ጊዜ ወደ ውጭ የማትልክበትና ወደ ውስጥ ማስገባት የማትችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

በፖለቲካዊ ዘርፍ ደግሞ እንደ ሃገር እውን የሆነ ሉዓላዊነት እንዲኖራት፣ ፖለቲካዊ ደህንነቷ እና ሃገራዊ ሚስጥሯ የተጠበቀ እንዲሆን የባህር በር ትልቅ ድርሻ ይጫወታል፡፡ የምታስገባቸው እቃዎች ወደብ በተከራይችበት ሃገራት እውቅናና ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡ በቀጠናው ላይ ያለውን ተሰሚነትና ሚና በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

ከወደብ ባለቤትነት ውጭ እንድትሆን የተደረገበት ዋናው መንገድ ኤርትራን በመገንጠል ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የአረብ ሃገራት ተሳትፎ ሲኖራቸው በተለይም ግብፅ ከፍተኛን ድርሻ ትይዛለች፡፡ ምዕራባዊያን ደግሞ እውቅና በመስጠት ድጋፍ አድርገዋል፡፡ ኤርትራ በተገነጠለችበት ወቅት ራሷ ነጻነቷን ሳታውጇ ግብጽ ቀድማ እውቅና የሰጠጭም ሃገር ነች፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኤርትራን የአረብ ሊግ ታዛቢ ሃገር እንድትሆን ድጋፍ አድርጋለች፡፡

እ.ኤ.አ. በ1952 ዓ.ም ኤርትራ በፌደረሽን ወደ ኢትዮጵያ ስትቀላቀል ከተቃወሙ ሃገራት መካል አንዷ ስትሆን ለኔ ትገባኛለች የሚል ጥያቄም አንስታ ነበር፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ለአረብ ሊግ ተላልፋ ልትሰጥ ይገባታል የሚል አቋምም አንጸባርቃለች፡፡ በዚህ ልክ ጠንክራ ስትከራከርና ስትደግፍ የነበረበት ዋናው ምክንያት በሁለቱ ሃገራት መካከል የተራዘመ ጦርነት በመፍጠር




በቀይ ባህር ዙሪያ የሚገኙ ሃገራት

ትኩረቷን ወደ አባይ እንዳታዞርና በብቸኝነት ለመጠቀም በመፈለጓ ነው፡፡

በቀይ ባህር ዙሪያ ያሉ ስምንት ሃገራት ማለትም ግብፅ፣ ሳውዲአረቢያ፣ሱዳና ሌሎች ሃገራት የቀይ ባህር ፎረምን( red sea forum) መስርተዋል፡፡ የፎረሙም መመስረት ያስፈለገበት ምክንያት በዙሪያው ካሉ ሃገራት መካካል ብዙ የህዝብ ቁጥር፣ የታሪክና የፖለቲካ ጥንካሬ ያላትንና ለቀይ ባህር ዋነኛ ስትራቴጂካዊ መገኛ የሆነችውን ኢትዮጵያን እንደስጋት በመቁጠር ነው፡፡ የአረብ ሃገራትና የአረብ ሊግ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሃገራትም ከፍተኛ ፍላጎትና ጥቅም አለን ብለው ስለሚያስቡ ኢትዮጵያን ከፎረሙ አባልነት እንድትገለል አድርገዋል፡፡ በብዙ ሺህ ማይል ርቀት ያሉ ሃገራት ወደ ቀይ ባህር በመዝለቅ የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ብዙ ጥረት ሲያደርጉ ኢትዮጵያ መቶ በማይሞላ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሆና ተጠቃሚ እንዳትሆን አድርጓታል፡፡

በአሁኑ ወቅት ጂኦፖለቲካዊና ጂኦስትራቴጂካዊ ጥቅሙ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት አዳዲስ የደህንነት ስጋቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ በተለይም የባህር ላይ ውንብድና፣ የሽብር ትግልና ድንበር ዘለል ወንጀለኞች ማለትም ህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የመሳሪያ ንግድ እና የአደንዛዥ እፅ ዝውውር መከናወኛ ቦታ በመሆኑ የሃገራትን ቀልብ ስቧል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባሕር ሕግ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የባህር በር የሌላቸው ሃገራት የባህር በርና የተፈጥሮ ሃብት እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በአለም አቀፍ ደረጃ ያለው ህግና መርህ ደካማ እና ሊያስፈፅም ሚችል አስገዳጅ ህግ የሌለው ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአፍሪካ ህብረትም ይህን ህግ በመጠቀም የባህር በር የሌላቸው ሃገራት በቅርበት የሚገኘውን ወደብ እንዲጠቀሙ ሲያስገድድ አይታይም፡፡ ስለሆነም ይህ አስገዳጅ ህግ የሚመሰረተው በሀገራት መልካም ፈቃድ ብቻ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ነገር ግን ጂኦፖለቲካዊና ጂኦስትራቴጅካዊ ንፅፅራዊ ጠቀሜታን በማስቀደምና ቀጠናዊ ውህደት ላይ ትኩረት ያደረገ አካሄድ በመከተል የባህር በር ተጠቃሚ መሆን ይችላል፡፡ በኢጋድ (IGAD) አማካኝነት ቀጠናዊ ትስስር በመፍጠር ከኬንያ እስከ ኤርትራ ድረስ ያሉ ወደቦችን መጠቀም የሚያስችል ስምምነት በመፈጸምና በወዳጅነት ላይ የተመሰረተ



**የኢትዮጵያ የጭነት መርከብ ጂቡቲ ወደብ ላይ**

ፖለቲካዊ አካሄድን በመከተል ተጠቃሚ መሆን ያደርጋል፡፡ ነገር ግን የባህር በር ካላቸው ሃገራት ፈቃድና ይሁንታ ውጭ በተፈቀደው አለም አቀፍ ህግ መሰረት ብቻ የባህር በር ማግኘት አይችልም፡፡

ከምፅዋ እስከ በርበራ ድረስ ያሉ ወደቦች በታሪክ የኢትዮጵያ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ነግር ግን ታሪካዊ ዳራ ብቻ በመያዝ ወደ እነዚህ ወደቦች መምጣት አያስችልም፡፡ ታሪኩ የሚጠቅመው የባህር በሩ ካላቸው ሃገራት ጋር በመነጋገርና ሰጥቶ በመቀበል መርህ በመተሳሰር ተጠቃሚ መሆን ያስችላል፡፡ ለአብነትም ጂቡቲ ከኢትዮጵያ 400 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይልና የንፁህ ውሃ አቅርቦት በመውሰድ ከወደብ ኪራይ ቅናሽ ታደርጋለች፡፡

ሌላው እንደ አማራጭ ተወስዶ የነበረው ከሱዳን ጋር ሲሆን ኦማር አልበሽር ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ወደብ በጋራ ለመጠቀም የሚያስችል ስምምነት ተደረሰ፡፡ ነገር ግን በመርህ ደረጃ ወይም በህግ አግባብ የተደገፈ ስላልነበር ተፈፃሚ ባለመሆኑ ምክንያት ፕረዚደንቱ ከስልጣን ሲወርድና በወታደራዊ አስተዳደር ሲተካ ስምምነቱ ዳር ሳይዝ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በወሰን ይገባኛልና በአባይ ጉዳይ አለመግባባት በመፈጠሩና በእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት ወደቡን መጠቀም አልተቻለም፡፡

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብዙ ጸሃፊያን "ቀይ ባህርና ምስራቅ አፍሪካ ስትራቴጅክ ማግኔት ናቸው" በማለት እንደፃፉ ታሪክ ያስረዳል፡፡ በተለይም የስዊዝ ቦይ መከፈቱን ተከትሎ ሶስቱን አህጉራት በማገናኘትና የረጅም ርቀት ጉዞን በማስቀረት የንግድ እንቅስቃሴው በፍጥነት እንዲያድግ አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያትም 40 በመቶ የሚሆነው የንግድ መተላለፊያ ቀጠና እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ብዙ ሃያላን ሃገራትም የራሳቸውን ፍላጎት ይዘው ወደ ቀጠናው በመምጣት ተሰባስበዋል፡፡ ይህን መስመር መቆጣጠር ከኢኮኖሚ፣ ከስትራቴጂ፣ ከሃገራት ገፅታ ግንባታና ተሰሚነት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በርካታ ቁጥር ያላቸው ከተለያዩ አቅጣጫ የመጡ ሃገራት የጦር መንድርና ወደብ እየገነቡ ይገኛሉ፡፡ ለወደብ እና ለጦር ሰፈር ግንባታ በሚያደርጉት ውድድር በቀጠናው ላሉ ሃገራት በአሉታዊ መንገድ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በተለይም በሰላም፣ በልማት እና በቀጠናዊ መረጋጋት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ እያስከተ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሽኩቻ ሲኖር የእጅ አዙር ጦርነት/ የውክልና ጦርነት በማስነሳት ቀጠናዊ መረጋጋት እንዳይኖር እና የህዝቦች መፈናቀል እንዲኖር በማድረግ በቀጠናው ላይ ከፍተኛ ቀውስ ይፈጠራል፡፡ለዚህ እንደ ማሳያ ብንወስድ ሱዳን የገባችበት የእርስ በርስ ጦርነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከአሜሪካ እስከ ቻይና፣ ከፈረንሳይ እስከ ሳውድአረቢያ፣ ከእንግሊዝ እስከ ኢራን፣ ከቱርክ እስከ እስራኤል ድረስ በቀይ ባህር ቀጠና የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሽኩቻ ውስጥ ገብተዋል፡፡ እነዚህ ሃገራት ወደብ መገንባታቸው በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ነገር ግን በዙሪያውም ይሁን በዓለምአቀፍ ያሉ ሃገሮች ወደ ቀይ ባህርና ምስራቅ አፍሪካ መምጣታቸው በአወንታዊ መንገድ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ እነዚህ ሃገራት መወዳደራቸው ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ ይሁንና ገለልተኛ የሆነ አካሄድ በመከተል ከሁለቱም ወገን የሚገኘውን ምቹ ሁኔታ በመውሰድ መጠቀም ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ለቻይና እና ቱርክ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት መዳረሻቸው ነች፡፡ ቻይናም የቻይና-አፍሪካ ግንኙነትን ለማጠናከር አንድ ቀበቶ አንድ መንገድ የሚል መርህ በመዘርጋት የኢንቨስትመንት መዳረሻዋን አስፍታለች፡፡ ይህ በመሆኑ ምክንያት በተለይም ምዕራባዊያን በዚህ ስምምነት መከፋት ያሳያሉ፡፡

አሜሪካ በብዙ የአፍሪካ ሃገራት ላይ ወታደራዊ የጦር ሰፈር ገንብታለች፡፡ በአሜሪካ-አፍሪካ ኮማንድ የሚመራው አፍሪኮም (AFRICOM) ከ27 በላይ የጦር ቤዝ(መንደር) በተለያየ የአፍሪካ ክፍል አለው፡፡ ይህ የጦር ሰፈር መገንባት በአፍሪካዊያን ላይ ከፍተኛ የሆነ ስጋት ፈጥሯል፡፡ የሰላም፣ የልማት፣ የፖለቲካና ደህንነት ጉዳይ፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ጠንካራ ህዝባዊ የሆነ መንግስት እንዳይመሰረትና ከተመሰረተም በመፈንቅለ መንግስት በማስወገድና የእነሱን ጉዳይ አስፈፃሚ

# ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር

ወደስልጣን በማምጣት የሃገራቸውን ሃብት አልምተው እንዳይጠቀሙ አድርጓል፡፡

የሃያላን አገራት በዚህ ቀጠና የጦር ቤዝ መገንባታቸው እና የመሰባሰባቸው ምክንያት የራሳቸውን ፍላጎት ለማራመድና ብሄራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እንዲሁም በኢንቨስትመንት ስም ያልተነካውን የአፍሪካን ሃብት ያለ ከልካይ ለመበዝበዝ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ወደ ቀይ ባህር የመጡበት ዋናው ጉዳያቸው ቀይ ባህር ላይ ያለውን ብሔራዊ ጥቅም ማለትም ዋና የንግድ መተላለፊያ መስመር መሆኑ፣ የነዳጅ፣ የወርቅና የአሳ ሃብት ለመጠቀም ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ይህ በመሆኑ ምክንያት በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ብዛት ያለው የህዝብ ቁጥር በመኖሩ ከሌሎች በበለጠ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ለኢትዮጵያ ብቸኛ መተላለፊያዋ ሃገር ጂቡቲ በመሆኗ እና የጎረቤት ሃገራት ወደቦች በሌሎች ሃገራት ወታደራዊ ጦር መከበቡ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ ቀጣይነትና ደህንነት ላይ ስጋት መሆኑ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ አሁን ባለው የሃይል አሰላለፍ በዚህ ከቀጠለ ጂቡቲን እንደ ሃገር ተደራድሮ ወደብ ማግኘት የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ኃያላኑ ሃገራት የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የመጡ በመሆናቸው በምጣኔ ሃብት፣ በሰላምና ደህንነት፣በሉዓላዊነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ ሁለቱ ውሃዎችን (አባይና ቀይ ባህር) የህልውና ምሰሶችና የሉዓላዊነት ማረጋገጫ በመሆናቸው ነገሮችን በአሉታዊና በአወንታዊ በመመዘን የተጠና ስልትና አካሄድ መያዝ በእጅጉ ያስፈልጋታል፡፡

በቀይ ባህር እንዲሁም በአፍሪካ ሃገራት በቻይናና በአሜሪካ መካከል የሚደረገው ቀዝቀዛ ጦርነት ግብግቡ ከፍተኛ ነው፡፡ ሁለተኛው ቀዝቃዛው ጦርነት በምስራቅ አፍሪካ ዙሪያ እና በቀይ ባህር ላይ በብዙ ዘርፉ ማለትም በኢኮኖሚ፣ በወታደራዊ፣ በርዕዮተ አለም እዲሁም የሃይል ጥምረት በመፍጠር እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ይህ ቀዝቃዛ ጦርነት ሶሺያሊዝምን ሊበራሊዝም እንዳሸነፈው ሁሉ አንዱ ጎራ አሸናፊ ሆኖ ሊጠናቀቅ ወይም ተመጣጣኝ ሃይል በመያዝ ባለበት ሊቀጥል የሚችልበት እድል ሊኖር ይችላል፡፡

የቀይ ባህር ፖለቲካ ከአፍሪካ ቀንድም አልፎ የመካከለኛው ምስራቅን ፖለቲካም እየናጠው ይገኛል፡፡ በተለይም አሜሪካ በፕረዚደንት ዶናልድ ትራንፕ አስተዳደር የእስራኤልንና የፍልስጤም ጉዳይ ይፈታል ተብሎ የመጣው የክፍለ ዘመኑ የሰላም ስምምነት የበለጠ ቀጠናውን ውጥረት ውስጥ ከቶታል፡፡ ውጥረቱን የበለጠ ከፍ ከማድረግ አልፎ ጦርነቱ ዉስጥ አሰገብቶ የሀይል አሰላለፍ በመፍጠር ፊት ለፊት እና የእጅ አዙር ጦርነት ውስጥ ይገኛል፡፡ ለአብነትም ሊባኖስ፣ ኢራን፣ የመንና አሜሪካ ከእስራኤልና ፍልስጤም ጎን ተሰልፈው ይገኛሉ ፡፡ የሃውቲ ዓማፂያንም መነሻቸውን የመን በማድረግ የአረቡን አለም በሁለት ጎራ በማሰለፍ ቀጠናው ውጥረት ውስጥ እንዲገባ አድርገዋል፡፡ ይህን ሃይል ለመከላከል በሚል የሃይል ጥመረት በመፍጠር በቀጠናው ዙሪያ ግዙፍ ወታደራዊ እንቅስቀሴ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በቀይ ባህር ዙሪያ እተደረገ ባለው ፉክክር ኢትዮጵያ ወደ መልካም አጋጣሚ መቀየር ከቻለች መጠቀም የምትችልባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ የምትገኝበት ጂኦስትራተጅካዊ መገኛና ያላት ጂኦፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በቀጠናው ካሉት ሃገራት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ነው፡፡ ከዚህ በፊት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በተደረገው ሂደት ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ፣ የወታደራዊና ሌሎች ተዛማጅ ድጋፍፎችን አግኝታለች፡፡ በመሆኑም ከፉክክሩ ተጠቃሚ ለመሆን እንዳለን ስልታዊ መገኛ፣ ጂኦፖለቲካዊ ጥቅምና ለእነርሱ እንደምንሰጠው ጥቅም ይወሰናል፡፡

በመጨረሻም መምህር እምቢአለ ምዕራባዊያንና በዙሪያው የሚገኙ የአረብ ሃገራት በአፍሪካ ቀንድና በቀይ ባህር ዙሪያ የመጡበትን ዓላማ በመረዳት ብሔራዊ ጥቅምንና ፍላጎታቸውን ማጥናት ተጋላጭነትን ይቀንሳል፡፡ የሚከተሉት መርህ ሰጥቶ መቀበል ስለሆነ በፖለቲካዊ ስትራቴጂክና በህግ አግባብ ተይዞ በጥንቃቄ ሊመራ ይገባል፡፡ ብሔራዊ ጥቅምን በማሻሻል፣ የሚመጣውን ጉዳትና ጥቅም ለማሳናስና ለማሳደግ በእጅጉ ይጠቅማል፡፡ ያም ሆነ ይህ በፖለቲካዊ አካሔድ ቋሚ ወዳጅና ጠላት ስለሌለ ጂኦስትራቴጂና ጂኦኢኮኖሚያዊ እውነታዎችን በመረዳት ከራስ ጋር አዛምዶ በየጊዜው በመቀያየር ብሔራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ እንደሚገባ ሃሳባቸውን አካፍለዋል፡፡

የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም መምህር እምቢአለን ስለሰጡት ማብራሪያ ከልብ እያመሰገን የባህር በር የህልውና ጉዳይ፣ የሉዓላዊነት ማስጠበቂያ፣ የልዕልና መሰረት እንዲሁም የደህነነት ማረጋገጫ በመሆኑ የውስጣዊ ችግርን በመፍታት ሃገራዊ አንድነትን በማፅናት የህዝቦችን ብሔራዊ ጥቅም ሊያስጠብቅ የሚችል ጠንካራ መንግስታዊ አስተዳደር በመገንባት ከዚህም ከዚያም በቀይ ባህር ዙሪያ የተሰባሰቡ ሃገራት በሉዓላዊነታችን ላይ ከፍተኛ ስጋት እንደሆኑ በሚገባ በመረዳት ካለፉት ሶስት አስርት ዓመታት በፊት ወደ ነበርንበት ተጠቀሚነት መመለስ ይዋል ይደር ሊባል ማይገባው ጉዳይ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ሊታወቅና መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል በማለት ሃሳባችን እናስተላልፋለ፡፡ ሰላም!!!



# “ሸማ በየፈርጁ...”

በይበልጣል መኮንን

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የሰው ልጅ ከነበረባቸው ቦታዎች አንዷ መሆኗ ይነገርላታል። ይህንኑ እውነታ በርካታ መረጃዎችና ማስረጃዎች በግልፅ የሚያስረዱት ጉዳይ ሆኖ የምናገኘው ነው፡፡ በዋናነትም የሰው ፍልሰት ጥናቶች ፣ የቅሪተ አካል ጥናቶችና ሌሎች የሳይንሳዊ ዘዴዎች ቀድመው ምስክርነታቸውን ያስቀመጡለት ነው፡፡ ይህን ጥንታዊ የሰው ልጅ መገኛን ተከትሎ የሀገራችን እድገት የሚያፋጥኑም ሆኑ የሚያግዙ በርካታ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎችና ጠቃሚ ተግባራት ተዳምረው በውስጣቸው ሳፋፌ ስራዎች ሲከወኑ አያሌ መቶ አመታት ተቆጥረዋል፡፡

ይሁን እንጅ “ፊተኞች ኃለኞች ይሆናሉ ”እንደሚባለው በስልጣኔ የመጀመሪያውን ማማ የተቆናጠጠች ሀገር ፣ ጥንታዊ የሰውልጆች መገኛ የነበረች ሀገር ፣ ሰፋፊ ግዛቶችን ይዛ ስታስተዳድር የቆየች ሀገር ፣ የቅኝ ገዥዎችን ብርቱ ክንድ አሳፍራ የመለሰች ሀገር በተለይም ደግሞ ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ ናቸው የሚባሉትን የመልካምድር አቀማመጥን የታደለች ሀገር በተለያዩ ጎታች በሆኑ የማህበራዊ ፣ የፖለቲካዊ እና የኢኮኖሚያዊ ችግሮች ብሎም በሌሎች ደራሽ በሆኑ የሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ተከባ ስትጨነቅ ማየት የተለመደ ተግባር እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ በዋናነት ጎታች የሆኑ ችግሮች ጎታች በሆኑ የመፍትሔ ሀሳቦች እየተሳቡ እና እየተዋጡ በመምጣታቸው የሚከሰቱ ናቸው፡፡ ለችግሮች አፋጣኝ የመፍትሔ ሀሳቦች እየተቀመጠላቸው ትርጉም ያለው ስራ ተጨባጭ በሆነ አሰራር አለመተካቱ ለተራዘመ ችግር መዳረጉ አይቀርም፡፡ በተባበረ ክንድ ችግሮችን ከስራቸው ነቅሎ ለመጣል የጋራ ተግባቦት እና መረዳዳት ያስፈልጋል፡፡

“መተባበር ቢኖር መረዳዳት ቢኖር የት ይደረስ ነበር” እንደተባለው ሸማ በየፈርጁ ይለበሳልና እንደ ሀገር በሚደረግ ማንኛውም አይነት ድጋፍና ትብብር በተናጠልም ሆነ በማህበር ተደራጅተን ለሀገር እድገት ግንባታ በምንወረውረው ጠጠር ሀገር ትገነባለች፡፡ የሀገር እድገት ይፋጠናል፡፡ የዜጎች ችግር ይፈታል፡፡ ህዝብ በጋራ ሲቆም የሀገር መሰረት ይፀናል፡፡ ሀገራት በምንግስታቸው ብርቱ ጥንካሬ ብቻ ችግራቸውን ፈተው አሁን ከደረሱበት የእድገት ማማላይ አልደረሱም፡፡ ይልቁንም ህዝቦች በግልም ሆነ በቡድን ተደራጅተው በሚያደረጉት ሰናይ ምግባሮች እንጅ፡፡

በዚህ መልክ በህዝብ ተሳትፎ ላይ መሰረታቸውን የጣሉ ሰናይ ምግባሮች ለሀገር እድገት ዋስትና ሲሆኑ ማስተዋል የተለመደ ነው፡፡ በሰናይ ምግባራቸው ግንባር ቀደም ተዋናኝ ሆነው ከሚጠቀሱት መካከል አጋር የልማት ድርጅቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ አጋር የልማት ድርጅቶች የዜጎችና የሀገር ህልውና ተጠብቆ እድገታቸው እንዲፋጠን በማድረግ በኩል ወሳኝ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡ የልማት ድርጅቶች የአንድ ሀገር የምጣኔ ሀብት ተወዳዳሪነቱ እንዲጠነከር እና ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ በኩል ሰፊውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው የልማት ድርጅቶች የሀገር ግንባታ ሂደቱ ላይ በጎ ሚናቸውን በመወጣት በኩል በቅንጅትና በአንድነት በመስራት ለሀገር ልማት፣ ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታና ለዘላቂ ሰላም አስፈላጊውንና የማይተካ ሚናቸው ከወቅታዊ ሁኔታው ጋር አገናዝበው መተግበር ሲችሉ ነው፡፡

ይህን እስመልክቶ ሐዲስ መጽሄት በዚህ ውር ዕትሟ በአማራ ክልል ያሉ እና በክልሉ መንግስት አስተዳደር ስር ቁጥጥር እየተደረገባቸው ወደ ስራ የገቡ የልማት ድርጅቶች የክልሉ ሕዝብ በተደጋጋሚ እያጋጠመው ካለው የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ብሎም ክልሉ ያለበትን ወቅታዊ የኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ቀድሞ ችግሮችን በመከላከል ፣ በመቆጣጠር እና በመደገፍ የተሰሩ ስራዎችን ጨምሮ እያበረከቱት ያለው አስተዋፅኦ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያደረገችውን ቆይታ እንካችሁ ትላለች፡፡ መልካም ንባብ፡፡

አቶ በላይነህ መዝገቡ የአብክመ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተወካይ ዳይሬክተር ናቸው፡፡ አቶ በላይነህ የክልሉ የልማት ድርጅቶች በሶስት ሰፋፊ የልማት ዘርፎች ላይ ተሰማርተው እየሰሩ መሆናቸውን ይገልፀሉ፡፡ እነዚህ በክልሉ መንግስት ቁጥጥር እየተደረገባቸው ከሚተዳደሩት ልማት ዘርፎች መካከል የኮንስትራክሽን ፣ የግብርና እና ሌሎች ቀሪዎቹ ደግሞ በአምራች ዘርፍ ውስጥ የተካተቱት ናቸው፡፡

የክልሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በቁጥር ደረጃ ወደ 12 ገዳማ የሚጠጉ እንደሆኑ እና በአሁኑ ጊዜ ያላቸው ጠቅላላ የሰው ኃይልም በየፕሮጀክቱ ያሉትን ጊዚያዊ፣ ሰብ ኮንትራትና የቀን ሰራተኞች ሳይጨምር በድምሩ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞችን አካተው ይዘዋል፡፡ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን በሚመለከትም ስድስት መቶ ሰባ ስምንት ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም አምስት መቶ አምሳ አራት ማሽነሪዎች ያሏቸው ናቸው፡፡

በኮንስትራክሽን የልማት ዘርፍ ከተሰማሩት የክልሉ የልማት ድርጅቶች ውስጥ የውሃ ስራዎች ኮርፖሬሽን ፣ የልህቀት የዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፣ የአማራ ህንፃ ስራዎች

# ልማት/ኢኮኖሚ



አቶ በላይነህ መዝገቡ

የአብክመ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተወካይ

ኮንስትራክሽን ድርጅት ፣ የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት እና የአማራ ቤቶች ልማት ድርጅት ይገኙበታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የመጠጥ ውሃና የመስኖ ልማት ስራዎች ቀዳሚውን ቦታ በስፋት ይዘው በትኩረት እየተተገበሩ ያሉ የልማት መስኮች ናቸው፡፡

የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት የውሃ ሃብት አቅምን በጥናት ለመለየትና ለመጠጥና ለመስኖ ልማት ለማዋል በሚደረግ ጥረት ከቀላል ጉድጓድ እስከ ጥልቅ ጉድጓድ፤ ከቀላል መስኖ ካናል እስከ ግድብ ድረስ ማልማት ተችሏል፡፡ በዚህ ዘርፍ የተሰሩ ስራዎች የክልሉ ቀኝ እጅ ከመሆን አልፈው አዲስ አበባን ጨምሮ ሌሎች ክልሎች በመግባት ሜጋ ፕሮጀክቶችን በውጤታማነት በመፈጸም የራሳቸውን አሻራ እያሳረፉ ነው፡፡ በቀጣይም ይህ ዘርፉ የሚጠይቀውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀምና የመፈፀም አቅሙን በማሳደግ በክልሉና ከክልላችን ውጭ በአገር ዓቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ በተለይም በምስራቅ አፍሪካ ደረጃ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በመፈፀም የውሃ ሃብት ልማትን በማሳደግ የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በትኩረት በመስራት ላይ መሆናቸውን አቶ በላይነህ ገልፀውልናል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በተሰማራበት የህንጻ ግንባታ ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ግንባታዎችን ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ በመገንባት ለክልላችንና ለሀገራችን የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ በርካታ ግንባታዎችን በመገንባት በዘርፉ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ይህ ዘርፍ በክልላችንና በሌሎች የአገራችን ክፍሎች እስካሁን ያልታዩ ከፍታ ያላቸው ህንፃዎችን ገንብቶ አንቱታን ያተረፉ ሲሆን በቀጣይም በተመረጡና የግል ባለሃብቶችን ሊያበረታታ በሚያስችል መልኩ በከተሞች የሚስተዋለውን የመኖሪያና የንግድ ቤት እጦት ለመፍታት የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ቀርፆ በከተሞቻችን በማስተግበር ለከተሞቻችን ዘመናዊ ዕድገት የራሳቸውን አሻራ ለማሳረፍ እየተረባረበ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የመንገድ መሰረተ ልማት ለማሟላት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የአስፖልት መንገድና ድልድዮችን እየገነባ ከክልሉ አልፎ የሀገራችን የመሠረተ ልማት ክፍተት በመሙላት ዘመን አይሽሬ የሆኑ አሻራዎችን በማሳረፍ ላይ በትኩረት እየሰሩ ነው፡፡

ከኮንስትራክሽኑ ዘርፍ በዘለለ የክልሉ መንግስት የተሰማራበት የልማት መስክ የግብርናው ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ የተካተቱት የአማራ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ ፣ የኮምበልቻ ዶሮ ሃብት ልማት ኢንተርኘራይዝ እና የአማራ ደን ኢንተርፕራይዝ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ የኮምበልቻ ዶሮ ሃብት ልማት ኢንተርኘራይዝ በክልሉ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለገጠር የድሃ ድሃ ወገኖች በማቅረብ በድህነት ቅነሳው ላይ ቁልፍ ሚና ከመጫወት ባሻገር የገብያ ክፍተቱንና የኑሮ ውድነቱን በዶሮና በእንቁላል አቅርቦት ለመፍታት ከፍተኛ ስራ እየሰራ ያለ ኢንተርኘራይዝ ነው፡፡ እነዚህ የግብርናው ዘርፍ የልማት ድርጅቶች የክልሉን የምርጥ ዘር አቅርቦት ሰባ በመቶ በላይ በጥራት ለማቅረብ ብሎም የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በመደረግ ላይ እየተረባረቡ ያሉ ናቸው፡፡

የግብርናው ዘርፍ ደንን በማልማት በኩል እድሜ ጠገብና ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሌላቸውን ደኖች በማስወገድና በኮመርሻል ደን በመተካት ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚያገለግሉ እንዲሁም የተሻለ ደን ባለባቸው አካባቢዎች ደን የኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዲኖረው በማድረግና ከዘርፉ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና ለከባቢ አየር ንብረት ለውጥ መሻሻል ጠቀሜታው የጎላ እንዲሆን ታስቦ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡ ይህን ታሳቢ ያደረገ የደን ምርጥ ዘር አቅርቦት ስራ በስፋት

# ልማት/ኢኮኖሚ

እየተከናወነ ነው፡፡ በአጠቃላይ እይታ ይህ የግብርና ዘርፍ በቀጣይ ዘመኑ የሚጠይቀውን የግብርና ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ አቅርቦቱን በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት አሻሽሎ በማቅረብ የክልላችን ብሎም የአገራችን የማምረት አቅም ለማሳደግ በጥልቀት እየሰራ እንደሆነ አቶ በላይነህ ገልፀውልናል፡፡

የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ከተሰማራበት የልማት ዘርፍ ሶስተኛውና የመጨረሻው የአምራች ዘርፍ ሲሆን በዚህ ልማት ዘርፍ ስር የአማራ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪና ማሽን ቴክኖሎጅ ልማት ኢንተርፕራይዝ ፣ የአማራ ፓይፕ ፋብሪካ ፣ የኤጂ ቧንቧ መገጣጠሚያ ፋብሪካ እና የጎሸ ሜዳ ቧንቧና ፕላስቲክ ማምረቻ ድርጅቶች ተካተዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ለቴክኖሎጂ ትራንስፎርሜሽንና ለግብርና ምርት የሚያገለግሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በማቅረብ የተለያዩ ችግር ፈች የሆኑ ፋብሪካዎችን ማልማት ፣ ትራንስፎርመር ጥገና ፣ ፋርም አምፕልመንት ፕላንትና ጀኔራል ፍሌክሴብል ማኑፋክቸሪንግ በማስገንባት የክልሉን አልፎ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ እጥረቶች ለመቅረፍ የሚያስችል ተሰፋ ሰጪ ውጤቶችን እያስመዘገበ ያለ ዘርፍ ነው፡፡

ዘርፉ ለቴክኖሎጂ ሽግግርም ሆነ በወጭና ገቢ ዙሪያ ጉልህ ድርሻውን ሲጫዎት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለተሰማሩ ሌሎች የክልላችንም ሆነ የሀገራችን ድርጅቶች የሚያጋጥሟቸውን ማነቆዎች ከመፍታት ባለፈ ለፋብሪካዎች በርካታ ግብዓቶችን በመቅረብ ላይ አልሞ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህም ተግባር በውጭ ምንዛሬ የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶችንና ግብዓቶችን በራስ አቅም እየፈቱ የመሄድ ልምድ እንዲዳብር እያደረገ ነው፡፡

በክልሉ መንግስት ስር እየተዳደሩ ያሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ክልሉ ባለፉት አራት አመታት ካሳለፋቸው ችግሮች አንጻር ሲታይ የልማት ድርጅቶች ባይኖሩ ኑሮ ምን ይሆን ነበር ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ ባለፉት አራት እና አምስት ተከታታይ ዓመታት በነበሩት ችግሮች ዳፋው በከፍተኛ ሁኔታ ያረፈባቸውና የመጀመሪያ ደረጃ ገፈት ቀማሾች የሆኑት እነዚሁ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ችግሮችን በማቃለል የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጥ ለማምጣትና ዓለምዓቀፍ ሁኔታውን ተረድቶ ህልውናን ከማስቀጠል ባለፈ ተወዳዳሪና ተመራጭ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

አሁን ክልሉ ከገጠመው ወቅታዊ ሁኔታ አንፃር ደግሞ የልማት ድርጅቶቹ የልማት ጦርነት ማካሄድ አስፈላጊም ብቻ ሳይሆን ግዴታ መሆኑን ተረድተው አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎች ያለፈውን ጊዜ በሚያካክስ መልኩ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

እንዲሁም የጸጥታ መደፍረስ ባለባቸው አካባቢዎችም ቢሆን የሐይማኖት አባቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን በመያዝ የአካባቢው ሰላም ወደነበረበት እንዲመለስና ልማት መቼም ቢሆን መቆም የሌለበት መሆኑን ተወያይቶ መግባባት ላይ በመድረስ ቆመው የነበሩ በርካታ ፕሮጀክቶች ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ በዚህ ሂደትም የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት አንገብጋቢ የህብረተሰቡ ጥያቄዎች የሆኑትንና የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠሩ የሚገኙት ተለይተው በልዩ ትኩረት እየተሰሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በችግር ውስጥ ሆነንም ቢሆን የህብረተሰቡን የመልማት ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ በመፍታትና ለመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት ላይ ከወትሮው በተለየ የቀውስ ጊዜ የልማት ስትራቴጂ በመንደፍ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡

የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች የተቋቋሙበት ዋና አላማ የክልሉን ህብረተሰብ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ከሆኑ አዳጋዎች መከላከልና በክልሉ ውስጥ ያለውን የልማት ክፍተት በመሙላት ህብረተሰቡን ዘላቂ ወደ ሆነ ሁለንተናዊ ልማት ማሸጋገር በመሆኑ በየትኛውም ክስተት ላይ ፈጥኖ ደራሽነታቸው የተመሰከረላቸው ናቸው ያሉት አቶ በላይነህ ፤ በዚህ መልክ የተቋቋሙት የልማት ድርጅቶች ዓላማ ያደረጉትን ዳር ለማድረስ ይረዳቸው ዘንድ የክልሉ ህዝብ ደራሽ ከሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አዳጋዎች ቀድሞ እንዲከላከልና እንዲቆጣጠር የሚያስችል የማህበራዊ ሃላፊነት /ዘርፍ ተሻጋሪ/ ተግባራት ማስፈጸሚያ የፖሊስ ሰነድ በአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በኩል ተዘጋጅቶ እንዲወርድ ተደርጓል፡፡

እነዚህ ተግባራት ልማት ድርጅቶች የማህበረሰቡን እና የመንግስትን ግንኙነትን በማጠናከር የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በደንበኞችና በባለድርሻ አካላት መካከል ታዓማኒነትን በማትረፍ ምርትና አገልግሎትን ማስተዋወቅ ፣ ገበያን ማስፋት እና ገቢን ማሳደግ ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት ክልላዊና አገራዊ ተሳትፎን ለማጎልበት የሚያስችሉ ሆነው የተቀረፁ መሆናቸውን የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም ወቅቱ በሚጠይቀው መሰረት ጠንካራ ሃገራዊ አንድነትን ለመፍጠር ለሚካሄዱ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቶች፣ በማህበረሰቡ ጤና አጠባበቅ፤ ለእንቦጭ አረም ማስወገድ፣ ድርቅ በተከሰተባቸው የአገራችን ክፍሎች ለሚገኙ ወገኖች፣ በመላ አገሪቱ ካለው የጸጥታ መደፍረስ ጋር በተገናኜ ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው በልዩ ልዩ የስደተኛ መጠለያ ካምፖች ለሚገኙ ዜጎች የሚሆኑ ልዩ ልዩ ደራሽ ምግቦች፣ አልባሳትና የህፃናት አልሚ ምግቦች፣ በሶስት ዙር ለተካሄደው የህልውና ዘመቻ፣ ለህጻናትና አረጋውያን፣ ለልዩ ልዩ አካባቢያዊና ማሕበራዊ ችግሮች በተለይም በኤች አይ ቪ ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት የገንዘብና የዓይነት ድጋፎች እየተደረጉ ሲሆን መሰል ድጋፎች ወደፊትም በእነዚህ የልማት ድርጅቶቹ አማካኝነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥሉ ነግረውናል፡፡

# ልማት/ኢኮኖሚ

ከዚህ ባለፈ ክልሉ እየተገበረው ካለው የስራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ የክልሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በየዓመቱ በቋሚ፣ በኮንትራት፣ በአውትሶርስና በቀን ስራ መልክ በአማካይ ከአርባ ሽህ በላይ ለሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል እየፈጠረ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለያዩ አካቢዎች በነበረው አለመረጋጋት የተፈናቀሉ በርካታ ሰራተኞች በልማት ድርጅቶቻችን እንዲቀጠሩ ተደርገዋል፡፡ በእነዚህና መሰል ተግባራት ለማህበረሰቡ ፈጥነው በመድረስ ያልተቆጠበ ዘርፈ ብዙ ድጋፎችን በማድረግ በኩል የክልሉ መንግስት ልማት ድርጅቶች ያልተገደበ አለኝታቸውን አሳይተዋል፡፡

በተለየ ሁኔታ ወቅታዊ ችግሮችን በተባበረ ክንድ ለመፍታት በተናጠልም ይሁን ከሌሎች ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የክልሉ መንግስት ሲጠይቅ ብቻ ሳይሆን ከክልሉ መንግስት ከፍተኛ አመራሮች ጋር ከወትሮው የተለየ የጠበቀ የግንኙነት በመፍጠር ምን እናግዝ ምን እንደገፍ በሚል የሰው ሀይል፣ ማሽነሪ፣ ተሽከርካሪ፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች ሁሉ ገብተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

የመንግስት ልማት ድርጅቶቻች በተለያ በረካታ ተግዳሮቶች እተፈተኑም ቢሆን በየተሰማሩበት ዘርፍ በክልላችን ብሎም በአገራችን አሁን ያለውን የመልማት ፍላጎት ያህል ማልማት የቻሉ ናቸው ባይባልም የክልሉን የልማት ክፍተት በመሙላት የህዝባችን መሠረታዊ ችግሮች በማቃለል በኩል ያላቸው ሚና በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፡፡ በቀጣይም ውስጣዊ ችግሮቻቸውን አርመው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማቸውን አሳድገው እስካሁን ከሚሰጡት የላቀ አገልግሎት በሙሉ አቅማቸው እንዲሰጡና የተቋቋሙበትን አላማ በሚገባ እንዲያሳኩ የሁሉንም አካል ድጋፍና እገዛ ይፈልጋሉ፡፡ የልማት ድርጅቶች ወቅቱ የሚጠይቀውን የቢዝነስ አስተሳሰብ፣ አደረጃጀትና አሠራር ተላብሰው ከክልላችን ባሻገር በሀገርና በሀጉር ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆነው የክልሉን የልማት ክፍተት እንዲሞሉና ሁለንተናዊ እድገትን የሚያፋጥኑ የሪፎርምና የመልሶ ማደራጀት ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ የተጀመሩ ስራዎች መሬት እንዲነኩ በየደረጃው የሚገኙ የበርካታ አካላት ድጋፍና ቀና ትብብርን የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ስለሆነም የክልሉ መንግስት አሁን ላይ ለልማት ድርጅቶቹ እየሰጠ ያለው ትኩረት እጅግ የሚያስመሰግን በመሆኑ ወደፊትም የበለጠ ቀረብ ብሎ መደገፍና መከታተል ቢችል፤ በየደረጃው የሚገኘው አመራር፣ የፍትህ ተቋማት፣ ወጣቱ፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ሌሎች ድርጅቶችና መላ ህብረተሰቡ ቅንጅታዊ አሰራርን የማጠናከር ስራዎችን እንዲሰራ፣ ለሚሰሩ ልማቶች ነቃፊ ከመሆን ወጥቶ ደጋፊ እንዲሆን፣ በልማት ድርጅቶች ላይ የሚስተዋለው ያልተገባ ጣልቃ ገብነት እንዲቆምና በድርጅቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የባለቤትነት ስሜት ማዳበር ሲሰሩ የማበረታታትና ሲያጠፉ የማስተካከል ባህል መዳበር አለበት፡፡ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ” በክልላችን ያለው የጸጥታ ሁኔታ የልማት ድርጅቶቹን በእጅጉ እየፈተናቸው የሚገኝ በመሆኑ ሁሉም የክልሉ ህዝብ ለሰላሙ ዘብ ቆመን ፊታችን ወደ ልማት በማዞር ክልላችን እናሻግር፡፡ የክልሉን ታላቅ ህዝብ ራዕይ በተግባር እናረጋግጥ ሲሉ ሀሳብ አስተያየታቸውን አጠቃለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል እንደሚባለው የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች በየተሰማሩባቸው የልማት ዘርፎች ሁሉ የክልሉን ሕዝብ የልማት ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ያላቸውን ዕውቀት፣ ጉልበት፣ ጊዜ እና ሀብት አሰባስበው ችግሮቻቸውን ለይተው የመፍታት ተግባር ላይ መሰማራት ለነገ የማይባል ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡ የክልሉ ህዝብ የበለጸገና ከችግር የፀዳ እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ ክልሉ ያሉበትን ክፍተቶች ለይተው ክፍተቱን ለመሙላት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ከሁሉም የልማት ድርጅቶች የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም ሸማ በየፈርጁ ይለበሳልና ልክልሉ መንግስትና ሕዝብ ያላችሁን አጋርነት በተግባር ማሳየት ተቀዳሚ ተግባር ላይ ትርጉም ያለው ስራ እና ለሌሎች ለክልሉ ሕዝብና መንግስት አርዕያ ሆኖ መገኘት ግድ ይላል፡፡ ለዚህ ደግሞ በእውነተኛ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ትብብርና ጥረት አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ የክልሉ ኢኮኖሚ በዘላቂነት ለመገንባት ብሎም ክልሉ እየገጠመው ያለውን ውቅታዊ ፣ የሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ አሰራሮችንና አደረጃጀቶችን ፈጥሮ በጋራ መንቀሳቀስ ከሁሉም የልማት ድርጅቶች የሚጠበቅ ተቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት እንላለን ሰላም፡፡

**ሁላችንም ለሰላሙ ዘብ ቁመን ፊታችንን ወደ ልማት በማዞር ክልላችን እናሻግር!!**

# ሰልፍና መድፍ

በይበልጣል መኮንን

ታሪክ ካለፈ በኋላ የሚነገር የትናንታዊ ትዝታ ሲኖረው አሁናዊ ህልም ነው፡፡ ታሪኩ በድርጊትነቱ ቢከስምም በፈጠረው ታሪክ እና በህሊናዊ እሳቤው የእውቀት መነሻ በመሆን ዘላለማዊ ሆኖ ይኖራል፡፡ በመሆኑም በታሪክ ታግለው ያታገሉ ጀግኖች የዛሬ ትግል የነገ ታሪክ ነው በሚል ዘመን አይሽሬ ታሪካቸውን አስቀምጠዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጀግኖችም ራሳቸውን ሰውተው ከማይሞተው ታሪካቸው ስር አይሞቴ ስማቸውን ተክለው ሲታወሱ ይኖራሉ፡፡

በታሪክ እንደሚታወቀው በጥቁሮች ምድር አፍሪካ የነጭ ወታደር ለዘመናት ዘምቶባት ነበር፡፡ በደልና መከራ የተፈራረቁባት አፍሪካ የጨለማ በርኖስ ተደፍቶባት ለአመታት ቆይታለች፡፡ በዚያ ዘመን ባለ ርስቶቹ እንግዳ ፣ እንግዶቹ ባለ ርስት ሆነው ነበር፡፡ ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካውያን ደጋሽና አንጋሽ ሆነው ቆይተውበታል፡፡ ወራሪዎቿ የብስ እያቋረጡ ባሕር እየሰነጠቁ ወደ ጥቁሯ ምድር ወታደሮቻቸውን ያለከልካይ አዝምተዋል፡፡ በነበራቸው ቆይታም በአፍሪካ አያሌ ግፎችን ፈፅመዋል፡፡ በዚያ ድንግዝግዝ በበዛበት የጨለማ ዘመን በነበረችው አፍሪካ በምሥራቁ ንፍቀ ክበብ ብርሃን ይታይ ነበር፡፡

ተስፋፊ ቅኝ ገዢዎችም በኢትዮጵያ የታየውን ደማቅ ብርሃን ለማጥፋት እንደሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት ከመቅደላ እስከ አድዋ፣ ከአድዋ እስከ ኡጋዴን ብርሃኗን ለማጥፋት ከፍተኛ ሙከራዎችን አድርገዋል፡፡ ኢትዮጵያን ለማፍረስና በእጅ አዙር ለመጠምዘዝ ብዙ ጦርነቶች ታውጀባታል፡፡ ብዙ ተመክሮባታል፡፡ የአባቱን ሽንፈት ለማካካስ ልጁ ይነሳል፤ ልጁ ሲሸነፍ የልጅ ልጅ እያለ ጠላት በኢትዮጵያውያን ክንድ ተመትቶ፣ በሰይፋቸው ተቀልቶ እና በጎራዴያቸው ተበልቶ እንዳልነበር ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ የአሸናፊነት መንፈስ የኢትዮጵያዊነት ጽናት እና አንድነት ነው፡፡ በሰፊው የሀገራችን ታሪክ ውስጥ መከፋቷ የከፉቸው፣ መነካቷ ያመማቸው ታሪክ የማይረሳቸው ጀግና ልጆች ነበሯት፡፡ ለክብሯ ደማቸውን አፍስሰውላታል፤ ለዳር ድንበሯ አጥንታቸውን ከስክሰውላታል፡፡ በዚህ ተጋድሏቸው የነጭን ክንድ በክንዳቸው ንደው የከፋታቸውን ግንብ አፍርሰዋል፡፡ እነዚህ "እምዬ" የምትመካባቸው፤ አፏን ሞልታ የምትጠራቸው ልጆቿ ግንባራቸውን እንጅ ጀርባቸውን ለጥይት አልሰጡም፡፡ ይህንንም ምስክርነት ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ አሁን ድረስ ለእናት ሀገር የተከፈለን ውድ ዋጋ አሳይተውናል፡፡ እኒህ አይበገሬ ልጆቿ የኢትዮጵያን ደማቅ የብርሃን ማኅተም በክንዳቸው አትመው ታሪክ አስቀጥለዋል፡፡ መሠረት ሆነው አፅንተዋታል፡፡

የኢትዮጵያ ጀግኖች ጨለማ አይበግራቸውም፣ ቸነፈር አይገታቸውም፣ ውሽንፍር ነጎድጓዱ አያስደነግጣቸውም፣ ይልቁንም ጨለማ በበዛበት ምድር ከፍ ብላ እንድታበራ አስችለዋታል፡፡ በጀግኖቿ ጽናት በጠበቀ አንድነት ፀንታ የቆመችውን ኢትዮጵያ የሚያጠፋትም ሆነ ከከፍታዋ የሚያወርዳት አንዳች ነገር አልነበረም፡፡ እነዚያ በቅኝ ግዛት አይናቸው የታወሩ ምዕራባውያን አሁንም በታሪኳ ይቀኑባታል ፤ በባህላዊ ዕሴቷ ይመቀኟታል ፤ በታወቀው ጽናቷ ይገረሙባታል፡፡

ኢትዮጵያ በግፍ የመጣባትን መቅጣትና በትዕቢት የነካትን መምታት ታውቅበታለች፡፡ ኢትዮጵያ ጠላት የማይደፍራት፣ ፈሪ የማይኖርባት የጀግኖች ሀገር መሆኗን በታሪክ አስመዝግባለች፡፡ አሁንም እንደ ቀደመው ዘመን ሁሉ ጠላቶቿ ተነስተውባታል፡፡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሀገራቸውን ሳያስደፍሩ የኖሩት ኢትዮጵያውያን ታዲያ በዘመኑ ለተነሳባቸው ጠላትም ዝም ብለው አልተቀመጡም፡፡ በጦርነት የመጣውን በጦርነት፤ በሐሰት የመጣውን በእውነት መልሰውታል፡፡

አጼ ቴዎድሮስ በዘመናዊ መንገድ የተደራጀ እና በስርዓት የሚመራ ዘመናዊ ጦር በመገንባት በኩል የወሰዱት ወሳኝ እርምጃ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ እንደሆነ በርካታ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ የውትድርና መሣሪያዎችን በሃገር ውስጥ ማምረት ከመቻል ጀምሮ ፣ ወታደራዊ ሣይንስን የተላበሰ አሰላለፍ እና ወቅታዊ መረጃ ለወታደራዊ አፈፃፀም ያለውን ጠቀሜታ ቀድመው ተረድተው ሳይንሳዊ ጥበብን የተላበሰ ጦር ለመገንባት አደረጃጀት ፈጥረዋል፡፡ ከእሳቸው ቀጥለው የመጡት ነገሥታትም ሆኑ መንግሥታት የራሳቸውን ማሻሻያዎች እያደረጉ አሁን ካለንበት ደረጃ ለማድረስ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዳበረከቱ መዛግብቱ በዝርዝር ያብራራሉ፡፡

በአጠቃላይ ሓዲስ መጽሄት በባህልና ታሪክ አምድ እትሟ በሠላሙ ጊዜ ገበሬ በጦርነት ጊዜ ጀግንነትን የተላበሰ የጦር ጀግና የማፍራቱን ምሥጢር እና የነበረውን ሂደት ለአንባቢያን እንካችሁ ትላለች፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ቀደም ሲል በጋሻ እና ጦር የተጀመረው የትጥቅ አደረጃጀት ምን ደረጃ እንደደረሰ ትቃኛለች፡፡ ያለፉት ነገሥታትና መንግሥታት ዘመናዊ ጦር በመገንባት በኩል ያደረጉትን ጥረት፣ ለውጦች እና የተደረጉ ማሻሻያዎችን ትዳስሳለች፡፡ እንዲሁም



"መሳሪያ እየገዙ መታጠቅ የአንድን ሀገር ትልቅነት አያሳይም፡፡"

አቶ መሰረት ወርቁ

በተደረጉት እልህ አስጨራሽ ውጊያዎች ውስጥ የተጠቀሟቸውን የጦር ትጥቆችና የነበራቸውን አሰላለፍ አሁን ለደረስንበት የውጊያ ጥበብ ያበረከተውን አስተዋፅኦ አጉልቶ በማሳየት የኢትዮጵያ ሳይንስ በውጊያ ጥበብ የደረሰበትን ደረጃ ለማስገንዘብ ከደብረ-ታቦር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁር ጋር የተደረገውን ቃለ-ምልልስ ተጋበዙ፡፡ መልካም ንባብ፡፡

ዘመነ መሳፍንት ከይኩኖ አምላክ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋርድ የመጣ ስርአት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የተለያዩ ባላባቶች የተንሰራፉበት፣ ሃይለኞች አገሪቱን ተቀራምተው የሚያስተዳድሩበት፣ ግብረ-ገብና ፖለቲካ ውጥንቅጡ የወጣበት ፣ ሁሉ በሁሉ ጦርነት የታወጀበት፣ በያካባቢው ያለማንም አንጋሽ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ምጣኔ ሳይኖር አሻንጉሊት የሆነ ንጉስ የነገሠበት ዘመን ነበር፡፡ አጼ ቴዎድሮስም በየአካባቢው ያለ ከልካይ የነገሡትን ንጉሦች ተራ በተራ በመውጋት አሸነፉ። ዘመነ መሳፍንትም እንዲያበቃ በማድረግ የራሳቸውን አሻራ አስቀመጡ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሀገሪቱ ከዘመነ መሳፍንት አገዛዝ ወደ ዘመናዊት ኢትዮጵያ እድትሻገር ጥረት የተጀመረው በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ነው ይላሉ የታሪክ ምሁሩ አቶ መሰረት ወርቁ፡፡ አቶ መሰረት በደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ በታሪክና ቅርስ አስተዳደር የታሪክ መምህርና በአለቃ ገብረ- ሃና ባህል ጥናት ዳይሬክቱቶሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡

አቶ መሰረት አጼ ቴዎድሮስን በንግሥና ዘመናቸው ታላቅ የለውጥ ጅማሮ ያስባላቸውን ታሪክ እንዲህ ይገልፁታል፡፡ ጊዜ በራሱ ሃያል ያደረጋቸው ንጉሥ አጼ ቴዎድሮስ ናቸው ይሏቸዋል፡፡ ከምንም በላይ የነበራቸው ራዕይ፣ የወቅቱ ባላባቶች ትርምስ፣ የግብረ-ገብ መላሸቅ፣ የቴክኖሎጂ ኋላቀርነት እና የአገሪቱን መኖር አለመኖር ጥያቄ ውስጥ የጣሉ ጉዳዮችን ቀድመው የተረዱ መሆናቸው ለየት ያደርጋቸዋል፡፡

አጼ ቴዎድሮስ ያወጇቸው ለውጦች፣ የተከተሏቸውና ሊተገብሯቸው የፈለጓቸው ፖሊሲዎች፣ ችግሮችን ቀድመው ተረድተው ለመፍታት ያሳዩት እልከኝነትና የነበራቸው ቁርጠኝነት፣ ለብሔራዊ ተሃድሶ የሰጡት ግምት፣ አገሪቱን ወደ ዘመናዊ አገር ለማሻገር የነበራቸው ህልም፣ የተንሰራፋውን የባሪያ ንግድ ለመከላከል ያደረጉት ጥረት፣ በአማርኛ ስነ ጽሁፍ ላይ ያደረጉት መሻሻል እና በአዲሱ ስርዓት መሰረት የግብር እና የፍርድ ባለስልጣናት ከማዕከላዊ መንግስት ደመወዛቸውን እንዲያገኙ ማስቻል የሚሉት መጠቀስ ያለባቸው መልካም ጅምሮች ነበሩ፡፡ ከምንም በላይ አንድ የሆነችና ጠንካራ ኢትዮጵያን በመፍጠር በኩል የነበራቸው ሚና፣ አንድነትን እና ስልጣኔን ማስተዋወቃቸው፣ ታላቅ የለውጥ ጀማሪ መሆናቸው እና ከጊዜው ቀድመው የሰለጠኑ ድንቅ መሪ አስብሏቸዋል፡፡ ለዚህም ደግሞ በቤተ-እምነት "የፍካሬ ኢየሱስ ገድል" እየሰሙ ማደጋቸው በወቅቱ ጠንካራ መሪ እዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል፡፡

ሌላው የጥንካሬያቸው እና የለውጣቸው ማሳያ የሆነው ወደ ላይ የሚያወጣቸውን መሰላል ቀድመው የተረዱ መሆናቸው ነበር፡፡ ይህም ብቸኛው መሰላል የውትድርና ብቃታቸው እንደሆነ ጠንቅቀው የተረዱ መሆናቸው ነው፡፡ በዚያም መንገድ አገራዊ ሠራዊቱን ለማጠናከርና ብሔራዊ አንድነትን እውን ለማድረግ የመጀመሪያውን ታላቅ ለውጥ ያስባላቸውን የመሰረት ድንጋይ ጣሉ፡፡ ይህ ታላቅ ለውጥ ሶስት አበይት ክፍሎች በመዋቅር፣ በዲሲፕሊንና በትጥቅ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

እነዚህ ለውጦች ከሞላ ጎደል የተወደዱና ለብዙ ድሎች ያበቋቸው ሲሆኑ ስልጣናቸውንም ለማንሰራፋት አይነተኛ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ ከመዋቅር አንጻር ያመጡት ለውጥ ከተለያዩ ክፍለ ሃገሮች የመጡት ወታደሮች በንጉሡ ነገሥቱ በተዋቀረ አንድ የጦር ክፍል ስር እንዲደራጁ ዕድል ፈጥሮላቸዋል። እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ሰራዊት የሚሰራበት የአስር አለቃ ፣ የሀምሳ አለቃና መሰል ማዕረጎች የተፈጠሩት በእርሳቸው ሲሆን ወታደሮች ቋሚ ደሞዝ ተቆርጦላቸው አላስፈላጊ የጉልበትና ገንዘብ ብዝበዛ



**አፄ ቴዎድሮስ ጋፋት ላይ ያሰሩት “ሴባስቶፖል መድፍ”**

የተከለከለው በእርሳቸው ዘመን ነበር፡፡ ሌላው ጉዳይ ንጉሡ በሠራዊቱ ዘንድ “እንደ ብረት የጠነከረ” ዲሲፕሊን ለማቋቋም ሞክረዋል። አብዛኛው የአጼ ቴዎድሮስ ሰራዊት የጦር መሳሪያ ከጦር ሜዳ የተማረከ ኋላቀር በመሆኑ ከአውሮጳ ቴክኖሎጂ በማስመጣት በኢትዮጵያ ምድር ላይ የመሳሪያ ማምረቻ ለማቋቋም ሞክረዋል።

አፄ ቴዎድሮስ የመጀመሪያው የዘመናዊ ጦር መሳሪያ የታጠቀ ውጊያ የገጠማቸው “ደበርኪ”ላይ ነበር ፡፡ (“ደበርኪ” የሚለው ቃል ያሁኗን ደባርቅ ያመለክታል)፡፡ ምንም እንኳ የርሳቸው ሃይሎች ከግብጾቹ ቢበልጡም በሙሃመድ አሊ የሚመራው የግብጽ ወራሪ ሀይል በዲሲፕሊን፣ በዘመናዊ ሰልፍና በመድፍ የሰለጠነ እና የታጠቀ ስለነበር አፄ ቴዎድሮስ ተሸነፉ። በወቅቱም የንጉሱ ሰራዊት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በመድፍ ተጨፈጨፈባቸው፡፡ ደበርኪ ላይ ታላቅ ሽንፈት የተባለውን ንጉሡ ተከናነቡ፡፡ ይህ ጉዳይ አፄ ቴዎድሮስን በእጅጉ ያሳዘነ ክስተት ብቻ ሆኖ አላለፈም ይልቁንም የአጼ ቴዎድሮስን መድፍ የመስራት ፍላጎት እንዲኖራቸው ረድቷቸዋል ይላሉ አቶ መሰረት፡፡

ከዚህ ክስተት በኋላ ነበር የአፄ ቴዎድሮስ ዘመናዊ የጦር መሳሪያን ለማግኘትና ዘመናዊ የጦር ስልትን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያሳደሩት። በመሆኑም ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ዘመናዊ የቴክኖሎጅ መንደርን በጋፋት መሰረቱ፡፡ ይህም ንጉሱ በዘመናቸው ታላቁን የቴክኖሎጅ ሽግግር ያደረጉበት ወሳኝ ጊዜ እንደነበር መምህሩ በአፅንዖት ይገልፃሉ፡፡ ጋፋት የኢንዱስትሪ የብርሃን ጨረር የተወረወረበት እና በአገራችን የኢንዱስትሪ ዘርፍ መሰረት የተጣለበት ታላቅ ቦታ ነበር ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡

የጋፋት ቴክኖሎጂ መንደር በደብረ-ታቦር ከተማ አስተዳደር በህሩይና አባ አረጋይ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ቦታው የቴዎድሮስን የዘመናዊነት አሻራ የሚያሳይ ሲሆን የኢንዱስትሪ መንደር እንዲሆን የተመረጠበትን ምክንያት ሲያብራሩ ቀደም ሲል በጋፋት “ጠቢባን” ወይም “ነገደ-ጋፋት” የሚባሉ ጎሳዎች ሰፍረውበት እንደነበር ይናገራሉ፡፡ “ነገደ-ጋፋት” በዕደ ጥበብ ሙያ ማለትም በብረታ ብረት፣ በሸክላ እና በሽመና ሥራ ላይ የተሰማሩ ነበሩ፡፡ እነዚህ ማህበረሰቦች በአካባቢው የሚገኙ የአፈር አይነቶችን ማለትም እንደ “ቆለይ” እና “ደረሂና” የተባሉ የአፈር አይነቶች የብረት ማእድን እንዳላቸው ቀድመው የተረዱ ነበሩና ለተለያዩ የእደ-ጥበብ ውጤቶች ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡ ንጉሠ ነገሥቱም እነዚህን የአካባቢውን ማህበረሰብ ከአውሮፖ ሚስዮናውያን እና ተጓዦች ጋር በማቀናጀት ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን ለማምረት ትምህርት ቤት አቋቁመው ነበር፡፡ የእነዚህን የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች እውቀትና ልምድ ለመጠቀም ፈልገው ቦታውን እንደመረጡት ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም በአካባቢው መድፎችን ለማምረት የሚያስችሉ ጥሬ ዕቃዎች በመኖራቸው፣ የአካባቢው ምቹ የአየር ሁኔታ፣ ውሃ እና ስትራቴጂካዊ አቀማመጡ ከሁሉም በላይ ቦታው ንጉሡ ለዋና ከተማነት ከመረጡት አካባቢ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ቦታውን ተመራጭ እንዳደረገው አቶ መሰረት በስፋት ያብራራሉ፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ለመድፍ ያላቸው አክብሮት እና ፍላጎት ደበርኪ ሜዳ ላይ ተፀንሶ “ሴባስቶፖል” በሚል የሰየሙትን መድፍ ጋፋት ፋብሪካ ላይ አሰሩ፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ከሩሲያ ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ መድፉን በሚሰሩበት ወቅትም ሩሲያ “ከክርሚያ” ጋር ጦርነት ላይ ነበረች፡፡ ጦርነቱ ይደረግበት የነበረው ከተማ ስያሜ “ሴባስቶፖል” ይባል ስለነበር የመድፉ ስያሜው ከዚህ ጋር የተያያዘ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

አቶ መሰረት እደሚሉት የደብረ-ታቦር ዩኒቨርሲቲ የአፄ ቴዎድሮስን የእውቀትና የቴክኖሎጂ ጥያቄዎች ለመመለስ እና የነበራቸውን ህልምና ፍላጎት ዳር ለማድረስ ዩኒቨርሲቲው የአፄ ቴዎድሮስን መድፍ አርማ አድርጎ እየተንቀሣቀሠ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ጋፋት የቴክኖሎጅ መንደር ተጠብቆ ወደ ቅርስነት እንዲቀየር እና እንዲጎበኝ በማድረግ በኩል ቦታውን አስከብሮ የተለያዩ ሎጅዎችንና መናፈሻዎችን ለማስገንባት አስቦ እየተሰራ ነው፡፡ እንደመነሻም የጋፋት ኢንዱስትሪ መንደር ያለበትን አካባቢ ፈራርሶ ደብዛው እንዳይጠፋ አካባቢው ታጥሮ ጥበቃ እየተደረገለት ይገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር

# ባህል/ታሪክ



ዳግማዊ ቴዎድሮስ

በምህንድስና ዘርፍ በቴክኖሎጅ የተሻለ ስራ እንዲሠራ እየተደረገ ሲሆን ለአብነትም አሁን በቅርቡ ዩኒቨርስቲው ያስወነጨፈው ሮኬት የጋፋትን ቴክኖሎጂ ለማስቀጠል ታልሞ የተከናወነ ማሳያ ነው፡፡ ዩኒቨርስቲው የቴክኖሎጂ ትምህርት ክፍል የቴክኖሎጂ ውጤት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው፡፡ በተጨማሪም ከመከላከያ ጋር በመሆን አካባቢው ላይ ቀድመው ይመረቱ የነበሩትን መሣሪያዎች እንዲመረቱ የሚያስችል ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ እነዚህ ጅማሮዎች የአፄ ቴዎድሮስን ራዕይ ለማስቀጠል በዩኒቨርሲቲው የታሰቡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ጋፋት የኢንዱስትሪ መንደር ቅርስ ሆኖ እዲያገለግል በክልሉ ብሎም በሃገር ውስጥ የቱሪስት መስሕብ ስፍራ እንዲሆን ተደርጎ እየተሰራ ነው፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ሀገሬን አላስደፍርም ብለው እስከ ሞት ድረስ የከፈሉትን መሥዋዕትነት፣ ያሳዩትን የጀግንነት ቁርጠኝነት እና የነበረውን ቅብብሎሽ ለማሳየት ከእርሳቸው በኋላ የነገሡ የኢትዮጵያ ነገሥታት እና መንግስታት በሀገር አንድነት የነበራቸው ሚና ተቀራራቢ ነበር፡፡ ለዚህም ማሳያ የአውሮፖውያንን የቅኝ ግዛት ፍላጎት ለመግታት በዶጋሊ ፤ በጉንደት፣ በጉራ ፣ በመተማ፣ በአምባ አላጌ፣ በመቀሌ፣ በዓድዋ፣በወልወል፣ በማይጨው፣ በአምስት ዓመቱ የጣሊያን ወረራ፣ በካራ ማራ፣ በሽራሮ አሁንም ቢሆን በወራሪው ሃይል በተደረገው የእጅ አዙር ጦርነት በጀግንነት በመዋጋት ሀገራችን በአፍሪካ ብቸኛዋ በቅኝ ያልተያዘች እና በጠላት ያልተንበረከከች ሀገር ሆና እስከ ዛሬ ድረስ እንድትዘልቅ ያስቻሉ አብነቶች መሆናቸውን ምሁሩ ያብራራሉ፡፡

ዘመናዊ መሣሪያዎችን በማምረት በኩል የነበረው ቅብብሎሽ ሲታይም አፄ ቴዎድሮስ የጀመሯቸውን ሙሉ በሙሉ ማስቀጠል አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም የነበሩት ነገስታትና መንግስታት የጦር መሳሪያዎችን ከማምረት ይልቅ በእርዳታ መልክ መቀበልን ምርጫቸው አድርገው ስለነበር ነው፡፡

ከጋፋት የኢንዱስትሪ መንደር ትምህርት በመነሳት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከአድዋ ድል በኋላ ሌላ ጦርነት ይመጣል የሚል እሳቤ ስላልነበራቸው ትኩረታቸው አደረጃጀት ላይ ቢሆንም ውጅግራና ወጨፎ ጠመንጃዎችንና ጥይቶችን አዲስ አባባ አካባቢ ማስመረት ቀጥለው ነበር፡፡ ከርሳቸው ቀጥለው ስልጣን ላይ የወጡት አፄ ኃይለ ሥላሴም ቢሆኑ ትኩረታቸው መሳሪያዎችን ከማምረት ይልቅ ወታደራዊ ስልጠና ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

የደርግ ሥርዓት ወታደራዊ አገዛዝን ይከተል ስለነበር ጠንካራ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ግንባታ ላይ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ከቀድሞ ሶቬት ኅብረት እና ከሌሎች ሀገራት ድጋፍ በመታገዝ ጋፋት የሚል ስያሜ በመስጠትና የጋፋት የጦር መሣሪያ ምሕንድስናን በማቋቋም የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን ማምረት ችሏል፡፡ ከደርግ በኋላ የመጣው ኢህአዴግም ቢሆን ትኩረቱ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ስለነበር በማምረቱ ጉዳይ ብዙም አልገፋበትም፡፡

አሁንም ቢሆን የሚታየው ይኸው ነው፡፡ ድሮንን ጨምሮ የተለያዩ መሳሪያዎችን እየገዛን ነው ያለነው፡፡ እንደ አቶ መሰረት ገለፃ አንድ ሀገር የምትፈራው መሳሪያ ገዝታ በመታጠቅ ሳይሆን በማምረቷ ነው፡፡ ለዚህም እንደምሳሌ ሩሲያና የሌሎች መሰል ሀገሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ሀገሮች የጦር መሳሪያዎችን ማምረት ስለቻሉ የሚጣሉባቸውን ማቀቦች ሁሉ አይፈሩም፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ የታጠቀቻቸው የጦር መሳሪያዎቿ ከተለያዩ ሀገሮች የተገዙ ከመሆናቸው የተነሳ ሀገሮች

በራሳቸው ግዜ ሊቆልፏቸው እና ሊቆጣጠሯቸው የሚችሏቸው በመሆናቸው በቻልነው መጠን በራሳችን አቅም ማምረት እስካልቻልን ድረስ ከጥገኝነት ነፃ መውጣት እንደማንችልም አክለው ይገልፃሉ፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ከአባቶች የወረሰው ታሪክ፣ የአኗኗሩ ባህሉ፣ እድገቱ እና እምነቱ ያጀገነው ህዝብ ነው፡፡ የነበሩት ነገሥታትና መንግስታትም ቢሆኑ በሀገር አንድነት በኩል የነበራቸው ሚና ተቀራራቢ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በእምነቱና በሀገሩ አይደራደርም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀገሩን እንደሚስት እና እንደእናት ስለሚያይ መቀበሪያው እንደሆነች አምኖ የሚታገል ህዝብ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በየጊዜው በሚቃጣባት የጦርነት ታሪክ ሁሉ በድል የማጠናቀቋ ጥበብ መሰረቱ ይኸው ነው፡፡ የኢትዮጵያዊ ማንነት በማንኛውም ሥርዓት ሊቆራረጥና ሊጠፋ የማይችል መንፈሣዊ ሀብት ነው፡፡ በጦርነት ሠዓት ጠላቱንም ሆነ ወዳጁን የሚረዳበት ርቀት፣ አስቦ አልሞ መነሳቱና ጠላት የሚያደርሰውን ጉዳት ቀድሞ በመረዳት የመከላከል ብቃቱ አሁንም ድረስ ያለ ጥበብ ነው፡፡ ሀገሩን ከሁለመናው ማንነቱ ጋር አገናኝቶ በቁርጠኝነት የሚዋጋ ሲሆን እኔ ተሠውቸ ቀጣዩ ትውልድ ይዳን ብሎ ራሱን የሚሰዋ ህዝብ እደሆነ ተመልክተናል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የታጠቀውን ወኔ ማንም ሀገር አልታጠቀውም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ውርደትን የሚፀየፍ ህዝብ መሆኑን በተለያዩ ጊዜ ምስክረነቱን አሳይቷል፡፡ ኢትዮጵያ ከሌለች ብሔር፣ሃይማኖት የለም ብሎ የሚያምን ህዝብ በመሆኑ የኢትዮጵያ የውጊያ ጥበብ እንዳለ እስከ ወዙ ሊቀጥል ችሏል፡፡

አሁን ድረስ እየተተገበሩ ያሉና ዘመን ያልሻራቸው በርካታ የትግል ጥበቦች አሉን፡፡ ህዝባዊነትን ያማከለው የሎጂስቲክስ አጠቃቀማችን አሁንም ስራላይ ሲውል ይታያል፡፡ የደፈጣ ውጊያ ስልት እየቀጠለ ያለ ጥበብ ነው፡፡ የኢትዮጲያ ህዝብ ሀገሩን የሚያይበት ጥበብ የተለየ በመሆኑ የጀግንነት ወኔው ከዛ የመነጨ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ አብሮ የዘለቀ ነው፡፡ ህዝባዊ ማዕበል በጉንደት፣በጉራ፣ በአድዋ እና በቅርቡ በተደረጉ ጦርነቶች ላይ ተግባር ላይ የዋለ የውጊያ ጥበብ ነው፡፡ከኢትዮጵያ የጦርነት ጥበቦች መካከል ወኔ ቀስቃሽ ፉከራ እና ሽለላዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ጣሊያን በአምስት ዓመቱ ወረራ ጊዜ አድዋ ላይ በምን እንደተሸነፈ አጥንቶ ስለመጣ የሚፎክሩ ኢትዮጵያዊያንን እያሳደደ ያጠፋ ነበር፡፡

ከቀድሞው ታሪክ በመነሳት አሁን ያለንበትን የእድገት ደረጃ የሚመጥን ሳይንሳዊ የጦር መሳሪያ አጠቃቀም፣ ግንባታና የውጊያ ጥበብ ቢኖረንም በሚፈለገው ልክ አይደለም ፡፡ አሁን ላይ ዘመን ተሻጋሪ ወታደራዊ ሳተላይት የለንም፡፡ ዘመናዊ መሣሪያወችን በማስታጠቅ በኩል ጅማሮ ቢኖርም ከዘመኑ ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡

በመጨረሻም አቶ መሰረት ዘመናዊ የጦር ግንባታና የውጊያ ጥበብን ለማስቀጠል መንግስት የጦር መሣሪያን ማምረት አለበት ይላሉ፡፡ አጼ ቴዎድሮስም ያደረጉት ይህንን ነው፡፡ አሁንም ጥሬ ዕቃ፣ ቴክኖሎጂው እና ያሉትን ምሁራን ተጠቅመን መሣሪያ ልናመርት ይገባል፡፡ መሳሪያ እየገዙ መታጠቅ የአንድን ሀገር ትልቅነት አያሳይም፡፡ የታሪክ ባለሙያዎች ታሪኩን እንናገራለን፣ የሚመለከተው ባለሙያ የአፈሩን እና የጥሬ ዕቃውን አይነት ይለያል፣ ኢንቨስተሮችና ባለሀብቶች በበጀት ይደግፋሉ እነዚህን ነገሮች በማሟላት ዘመኑ የደረሰበትን የጦር መሳሪያ መገንባት ይቻላል፡፡ ታሪኮችን ሰንዶ መያዝ እና ለትውልድ ማስረፅ፣ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ባህልና ቅርሶችን የማጥናትና ጠብቆ የመያዝ ኀላፊነት ይኖርበታል፡፡ ታሪኩን መንገር ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከየት ወዴት እየሄደ እንደሆነ ለይቶ ማሳየት፣ መተንተን፣ መሰነድ እና የተለያዩ ጉዳዩችን በመዳሰስ የሀገርን እንቅስቃሴ ማሳየት የሚዲያው ተግባር ነው፡፡ መረጃን ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ እና ህዝብን በማንቃት በኩል የጋዜጠኞች ሚና ከፍ ያለ በመሆኑ ሚዲያው ወጣ ያለ እይታ በመፈለግ አንባቢያን ማስገንዘብ ኖርበታል፡፡

እኛ በራሰችን ለመቆም እና የራሳችን የጦር መሳሪያ ለማምረት ወደ ውስጣችን መመልከት ይገባል ያሉት መምህሩ ዛሬ የኛ ወዳጅ ሆነው የጦር መሳሪያ የሸጡልን ሀገሮች ነገ የኛ ጠላቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የውጭ ናፋቂ ሆነን ሀገር ልናስቀጥል አንችልም፡፡ ሁላችንም መምህራን፣ጋዜጠኞች፣መንግስት፣ ባለሀብቱ፣ መካኒኩ እና ሌሎችም የድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል፡፡ ይህ ጉዳይም መሪ ላይ ብቻ የምንተወው አይደለም በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም የኢትዮጵያ ህዝብ በሀገሩና በማንነቱ የማይደራደር፣ የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፆታ፣ የዕውቀት እና የሀብት ልዩነት ያልፈተኑት መንፈሣዊ ሀብት የነበረው ኩሩ ህዝብ ቢሆንም አሁን ላይ ይህንን ታላቅ እሴት ማጣቱን ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያዊነት የተጋመደውን አንድነት ወደ ነበረበት የታሪክ ከፍታ ለመመለስ የነበረንን ታሪክ መለስ ብሎ መቃኘት አስፈላጊ እደሆነ ያምናል፡፡

ስለሆነም ከዜሮ መጀመር ከሚባለው አባዜ ወጥተን ካለፉት ነገሥታትና መንግስታት የማይጠቅመውን ትተን፤ የተሸለውን እንውሰድ፡፡ ወደ ውስጣችን ተመልክተን መቀጠል ያለበትን እናስቀጥል፡፡ ከቸልተኝነት እና ከምናገባኝ ክፉ እሳቤ ተላቀን ሀገርን እያስቀደመን የአባቶቻችንን የቤት ስራ ዳር እናድርስ፡፡ ሀገርን ማስቀጠል የሁላችንም የትውልዱ ግዴታ መሆኑን እንረዳ ፡፡ ሰላም፡፡

# ክፍያ ጭማሪና የወላጆች ስሜት

በደፋሩ እምሬ

ትምህርት የተማረ ህብረተሰብ በመፍጠርና አገርን በሁለንተናዊ መልኩ በማሳደግ በኩል የማይተካ ሚና አለው፡፡ ሚናውን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ትልቅ የገንዘብ መጠን፣ሰፊ የተማረ የሰው ሀይልና ጠንካራ አመራር ይፈልጋል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ብዙ የህዝብ ቁጥርና ሰፊ የቆዳ ሽፋን ላላት አገር ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስከፍለው ዋጋ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡

ህዝብ የትምህርት አገልግሎትን በጥራትና በቀላሉ ቀዬው ድረስ እንዲያገኝ ትልቁን ድርሻና ሀላፊነት የሚወሰደው መንግስት ቢሆንም ብቻውን ሰርቶ የሚያሳካው ስለማይሆን አጋር አካላት ያስፈልጉታል፡፡ በመሆኑም ትምህርትን ለግሉ ዘርፍ ክፍት በማድረግ ገብተው እንዲያለሙ መንግስት የፈጠረው አሰራር መጠነኛ አፎይታ እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡ ከዚህ አኳያ ዛሬ ላይ በአማራ ክልል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የግል ት/ቤቶች በዘርፉ ተሰማርተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ የግል ትምህርት ተቋማቱ የፈጠሩት ሰፊ የስራ እድል፣ የሚያስተናግዱት ተማሪ ቁጥር፣ ለትምህርት ስራው የሚውለው በቢሊዮን የሚገመት ገንዘብ ለመንግስት ትልቅ እገዛ ነው፡፡

ውድ አንባቢዎቻችን ከላይ በቀረበው ሀሳብ መነሻነት ቀጥሎ ልናስነብባችሁ የወደድነው በባህርዳር ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ የግል ት/ቤቶች መካከል አንድ ለአብነት መርጠን የ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ዝግጅትና አጀማመር፣የትምህርት ክፍያ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በሚመለከት ከተመረጠው የግል ት/ ቤት ስራ አስኪያጅ፣ከወላጆች ተወካይ እና ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ መረጃ ሰብስበን ለንባብ በሚመች




"ት/ቤታችን በትምህርት ጥራት ላይ አይደራደርም"

አቶ እሸቱ አሊ

መልኩ ያዘጋጀነውን ጽሁፍ ነው - መልካም ንባብ፡፡

በባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ውስጥ 121 የግል ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ 66 የሚሆኑት አፀደ ህፃናት፣ 45 ያህሉ አንደኛ ደረጃ እና 10ሩ ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የግል ትምህርት ቤቶች መካከል የወይዘሮ አየለች ደገፉ መታሰቢያ (አትሌት ሀይሌ ገ/ስላሴ) ት/ቤት አንዱ ነው፡፡ ይህ ት/ቤት ለ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ለመምህራን ሙያዊ ስልጠና በመስጠት፣ የተጓደኘ መምህራን ቅጥር በመፈፀም፣ አስፈላጊ የትምህርት ግብዓቶችን በማሟላት፣ ግቢ በማስዋብ፣ እና ሌሎችንም የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቶ መስከረም 14 ቀን መማር ማስተማሩን ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንደጀመረ የት/ቤቱ ስራ አስኪያጅ አቶ እሸቱ አሊ ነግረውናል፡፡

የግል ትምህርት ቤቶች ምንም እንኳን ትርፍን አስበው በትምህርት ላይ ለመስራት የተሰማሩ ቢሆንም ለወገናቸው ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ በኩል የድርሻቸውን እያበረከቱ ስለሆነ በመልካም ተግባር ይያዝላቸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ትምህርት ቤቶች የሚታሙበትና በየትምህርት አመቱ በተማሪ ወላጆች ዘንድ አቧራ እያስነሳ ያለው አነጋጋሪ ጉዳይ የክፍያ ጭማሪ ነው፡፡ የግል ት/ቤቶች ለአመቱ ትምህርት ዘመን ስራ የበጀታቸው ምንጭ የሚያርፈው በተማሪ ወላጆች ትከሻ ላይ ስለሚሆን ጭማሪ ማድረጋቸው አይቀሬ ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ጉዳይ መቼና ለምን



ወላጆች የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን መክፈቻ ስነስርአት ሲያካሂዱ(ወ/ሮ አየለች ደገፉ ት/ቤት ሽምብጥ ቀበሌ )

ክፍያ ጭማሪ እንደሚያደርጉ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ይህን አስመልክቶ ስራ አስኪያጇ ሲያብራሉ "ት/ቤታቸው የክፍያ ጭማሪ የሚያደርገው በየሶስት ዓመቱ ት/ቢሮና ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ባስቀመጡት ህግና መመሪያ መሰረት ነው፡፡ የትምህርት ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ በመማር ማስተማር አጠቃላይ ስራ ዙሪያ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትን ከሚያስፈልጋቸው በጀት ጋር ከለየ በኋላ የክፍያ ጭማሪው ምን ያህል መሆን እንዳለበት ይወስናል፡፡ የወላጅ ኮሚቴዎች ተጠርተው የማኔጅመንቱ ውሳኔ ሪፖርት ቀርቦላቸው በጥልቀት ገምግመው ተገቢውን አስተያየት ሰጥተውበት ከት/ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ ጋር መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ ወላጆች ይጠራሉ፡፡ ወላጆች ያሉበት ስብሰባ ሲካሄድ ከት/ቢሮና ከከተማ አስተዳደሩ ትምህርት መምሪያ ተወካዮች ይገኛሉ፡፡ሁሉም ወላጆች መገኘት ስላለባቸው ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ ወላጆቹም በሚቀርብላቸው የክፍያ ጭማሪ ዝርዝር ሪፖርት ላይ በጥልቀት መክረውና ዘክረው ይህ ይቀነስልን፣ ይህ ለምን ሆነ፤ ይህ አቅማችን ያገናዘበ አይደለም፤ወዘተ. የሚሉ አስተያየቶችን ከሰጡ በኋላ በክፍያ ጭማሪው መጠን ላይ የመጨረሻ ስምምነት በመፍጠር ይጠናቀቃል፡፡ የክፍያ ጭማሪ የሚደረገው ይህን ሁሉ ሂደት አልፎ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ስለሆነ የወ/ሮ አየለች ደገፉ መታሰቢያ ት/ቤት ወላጆች ቅሬታ የላቸውም፡፡ በመሠረቱ የት/ቤቱ ክፍያ ጭማሪ ከሌሎች አቻ የግል ት/ቤቶች ጋር ሲነጻፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ት/ቤቱ የማህበረሰብ ት/ቤት ስለሆነ በወላጆች ኑሮ ላይ ጫና የሚፈጥር ጭማሪ አያደርግም፡፡ የክፍያ ጭማሪ የሚደረገው ለመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ደመወዝ ለመጨመር፣ለመማር ማስተማር ስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ለማሟላት እና የት/ቤቱን ሁለንተናዊ አካባቢ ለማስዋብ የሚሉ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች መሰረት ተደርገው ነው እንጅ ትልቅ ትርፍ ለመሰብሰብ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ከዚህ ዓመት የክፍያ ጭማሪ ለመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች 15 በመቶ ደመወዝ ጭማሪ ተደርጐላቸዋል፡፡

ግብዓቶችን ከማሟላት አኳያም ከአጸደ ህጻናት (ኬጅ) እስከ 12ኛ ክፍል ላለው የመማር ማስተማር ስራ አስፈላጊ የሆኑ እንደ ላቦራቶሪ ማሟላት፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ግዥ፣ የመማሪያ ክፍሎች ማስዋብ፣ ወንበርና ጠረጴዛ ማሟላት፣ የመዝናኛና ስፖርት ቦታዎችን ማስተካከል፣ወዘተ. ተሰርተዋል፡፡ እነዚህ ተግባራት መፈፃማቸውንና ት/ቤቱ የገባውን ቃል አክብሮ እየሰራ መሆኑን የወላጅ ኮሚቴዎችና ወላጆች በአካል በት/ቤቱ ተገኝተው እንዲመለከቱና እንዲገመግሙ በማድረግ የሚያረጋግጡበትን አሰራር ት/ቤቱ አመቻችቷል" ብለዋል፡፡

ለወ/ሮ አየለች ደገፉ መታሰቢያ የግል ት/ቤት ስራ አስኪያጅ ያቀረብንላቸው ሌላው ጥያቄ ከምታደርጉት ክፍያ ባሻገር ለትምህርት ጥራት ምን ያህል ትኩረት ሰጥታችሁ ትሰራላችሁ የሚል ነው፡፡ እሳቸውም "ምንም እንኳን ት/ቤቱ ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ቢሆንም በትምህርት ጥራት ላይ አይደራደርም፡፡ እያስተማርን ያለነው ትውልድ(ሰው) ነው፡፡ በዕውቀት፣ በስነ-ምግባርና በሌሎች ክህሎቶች በደንብ የተገነባ ትውልድ እንዲፈጠር መስራት አለብን፡፡ ወፍራም ትርፍ ማግበስበስን ብቻ እያሰብን ዋናውን ጉዳይ ረስተን በአገርና በትውልድ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት መፈጸም አንፈልግም፡፡ ት/ቤታችን ለትምህርት ጥራት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሆነ ለማረጋገጥ የ2016 ዓ.ም ት/ት ዘመን ስራዎችን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የት/ት ጥራትን ለማረጋገጥ የመምህራንን አቅም መገንባት አንዱ ስልት ስለሆነ ት/ት ከመጀመሩ በፊት ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር በመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ ዙሪያ ለመምህራን ስልጠና ሰጥተናል፡፡ ብቃት ያላቸውን ተጓዳኝ መምህራን በቅጥር አሟልተናል፡፡ ሌላው የተሟላና ምቹ የትምህርት አካባቢ መፍጠር ለትምህርት ጥራት ወሳኝ በመሆኑ ከአጸደ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ሁሉ የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡ ይሁን እንጅ የትምህርት ጥራትን እየተገዳደሩብን ያሉ ክፍተቶች አሁንም ስላሉ እነሱን መሙላት ላይ ትኩረት ሰጥተን መስራታችን እንቀጥላለን" በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡



"የወላጆችን የተሳትፎ መብት አክብሮ የሚንቀሳቀስ ት/ቤት በመሆኑ ለሌሎች አቻ የግል ት/ቤቶች ተምሳሌት የሚሆን ነው"

አቶ በቃሉ መላኩ

አቶ እሸቱ ገለጻቸውን የቋጩት "ትምህርት ትውልድ የሚገነባበት መሳሪያ በመሆኑ ትርፍ እየታሰበ እንደሸቀጥ እንዳይታይ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ የወ/ሮ አየለች ደገፋ መታሰቢያ ት/ቤት ብዙ ትርፍ ይቅርብኝ ብሎ ከፍለው መማር የማይችሉ ከ250 በላይ ልጆችን በነጻ ያስተምራል፡፡ የት/ቤቱ መምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ሁለት ልጆቻቸውን በነጻ እንዲማሩ ፈቅዷል፡፡ የት/ቤታችን ተማሪዎች የነበሩና ዩኒቨርስቲ ገብተው የተመረቁትን በሀይሌና ዓለም ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው እንዲሰሩ ይመቻችላቸዋል፡፡ እነዚህና ሌሎች አስተማሪ የሆኑ የወ/ሮ አየለች ደገፋ መታሰቢያ ት/ቤት መልካም ተግባራት ለሌሎች አቻ የግል ት/ቤቶች ጥሩ ተሞክሮ ስለሚሆኑ ወስደው ቢተገብሯቸው መልካም ስምን በተግባር እየገነቡ ለወገን ስራ እድል በመፍጠር የዜግነት ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ማስመስከር ይችላሉ" የሚል መልዕክት በማስተላለፍ ነው፡፡

የትምህርት ቤቱን ወላጆች ወክለው አስተያየታቸውን ያጋሩን ሌላው የመረጃ ምንጫችን አቶ በቃሉ መላኩ ይባላሉ፡፡ ወላጆች በክፍያ ጭማሪ ላይ ያላቸው የመወያየትና የመወሰን መብታቸው ምን እንደሚመስል፣ ስለክፍያ ጭማሪው ያላቸው ስሜታና አስተያየት እንዲሁም ወላጆች የሚከፍሉት ክፍያ ለትምህርት ስራው በአግባቡ እየዋለ ስለመሆኑ የሚገመግሙበት አሰራር ምን እንደሚመስል ጠይቀናቸው ቀጥሎ የቀረበውን አስተያየት ሰጥተውናል፡፡

የወ/ሮ አየለች ገደፋ መታሰቢያ ት/ቤት ወላጆች በክፍያ ጭማሪና በሌሎችም የመማር ማስተማር ጉዳዮች ላይ በንቃት እንዲወያዩና እንዲወስኑ የሚያስችል ትልቅ እድል አላቸው፡፡ ት/ቤቱ "ማንን ይዞ ጉዞ" የሚል ጽኑ አቋምና አክብሮት አለው፡፡ በመሆኑም ወላጆች ያልተሳተፉበት፣ ያላመኑበትና ያልወሰኑበት አንዳች ምክንያትና የክፍያ ጭማሪ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ በዚህ ልክ የወላጆችን የተሳትፎ መብት አክብሮ የሚንቀሳቀስ ት/ቤት በመሆኑ ለሌሎች አቻ የግል ት/ቤቶች ተምሳሌት የሚሆን ነው፡፡

የወ/ሮ አየለች ደገፋ መታሰቢያ ት/ቤት ዘንድሮ የክፍያ ጭማሪ አድርጓል፡፡ ክፍያ ጭማሪው ሲደረግ የት/ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ፣የወላጅ ተወካዮችና ወላጆች በተናጠልና በጋራ ጥልቅ ውይይት አድርገውበታል፡፡ ሂደቱን ስንመለከት የክፍያ ጭማሪ መነሻ እቅድ የቀረበው ከት/ቤቱ ማኔጅመንት ኮሚቴ ነው፡፡ ኮሚቴውም ከመማር ማስተማሩ ስራ ጋር የተያያዙ በርካታ ዝርዝር ተግባራትን ወጭ ደምሮና ቀንሶ 30 በመቶ የክፍያ ጭማሪ እንዲደረግ ወስኖ ለወላጅ ተወካዮች አቀረበ፡፡ የወላጅ ተወካዮችም የቀረበላቸውን የክፍያ መነሻ ውሳኔ ከወቅቱ የኑሮ ውድነትና ወላጆች ካላቸው የመክፈል አቅም አንጻር እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ስራ ለማስቀጠል የሚያስፈልገውን በጀት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ጥልቅ ውይይት በማድረግ 15 በመቶ የክፍያ ጭማሪ መደረግ እንዳለበት ወሰኑ፡፡ የወላጅ ተወካዮች ይህን ውሳኔ ይዘው ከማኔጅመንት ኮሚቴው ጋር በጥልቀት መከረውበት የወላጅ ተወካዮች ውሳኔ ተቀባይነት አግኝቶ አጠቃላይ ወላጆች እንዲወያዩበት ቀረበላቸው፡፡ ወላጆችም የቀረበላቸውን የክፍያ ጭማሪ ሪፖርት በደንብ መርምረው፣ ከራሳቸው የመክፈል አቅም እኳያ እንዲሁም ለት/ቤቱ ማስተማር ስራ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ወጭ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ታሳቢ አድርገው የ2016 ዓ.ም ክፍያ ጭማሪ 15 በመቶ ሆኖ እንዲጸድቅና እንዲፈጸም ተስማማተው ወስነዋል፡፡ በመሆኑም በዘንድሮው የክፍያ



“የግል ት/ቤቶች ቅድሚያ ለትውልድ ሰጥተውና ለቃላቸው ታማኝ ሆነው ሊሰሩ ይገባቸዋል”

አቶ ደረጀ እስከዚያ

ጭማሪ ላይ ወላጆች ጥሩ አስተያየት አላቸው:: ይህ እንደተጠበቃ ሆኖ በጣት የሚቆጠሩ ወላጆች በዛብን በሚል እና ኢ-ምክንያታዊ የሆነ ውሃ የማይቋጥር ቅሬታ አቅርበው እንደገና ከት/ቤቱ ማኔጅመንትና ወላጅ ተወካዮች ጋር ውይይት አድርገው መተማመን ላይ ደርሰው ብዙሃኑ ወላጆች ተስማምተው ያጸደቁትን የክፍያ ውሳኔ ተቀብለው ቀጥለዋል::

የወ/ሮ አየለች ደገፉ መታሰቢያ ት/ቤት ወላጆች በክፍያ ጭማሪ ውሳኔ ላይ እንደሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ ሁሉ የትምህርት ስራው እንዴት እየተሰራ እንደሆነና የከፈሉት ክፍያም በአግባቡ ስራ ላይ እየዋለ ስለመሆኑ ትኩረት ሰጥተው ይከታተላሉ:: ለዚህ ስራ እንዲመችም በወር፣በሳምንታትና በአመት የሚገመግሙበት አሰራር ተዘርግቶላቸዋል:: እነዚህን የመገምገሚያ እድሎች ተጠቅመው የሚያስተውሏቸውን መልካም ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ የአሰራር ክፍተትና ብልሽት የሚስተዋልባቸው ተግባራት ወይም ንብረቶች ካሉ በፍጥነት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ጠንከር ያለ አስተያየት ይሰጣሉ ብለዋል::

አቶ በቃሉ ገለጻቸውን የቋጩት ት/ቤቱ፣መምህራን፣ወላጆች እና ተማሪዎች የተሰጣቸውን የስራ ድርሻና ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው ምክረ ሀሳብ በማቅረብ ነው:: በምክረ ሀሳቡ ት/ቤቱ ክፍያ ጭማሪ ላይ እንደሚያደርገው ትኩረት ሁሉ ለትምህርት ጥራትና ትውልድ ግንባታም ትልቅ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል:: ወላጆችም ብር መክፈል ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸው በአግባቡ እየተማሩ መሆኑን፣ ስነ-ምግባራቸው ምን እንደሚመስል፣ወዘተ. ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል:: መምህራን የልጆችን ጊዜ ሳያበክኑ ማስተማሩ ላይ በማዋል ተማሪዎች ጥሩ እውቀት እንዲይዙ ከመደበኛው ክፍለ ጊዜ በተጨማሪ የማካካሻ ትምህርት በመስጠት አጋዥ ጥያቄ ወረቀቶችን በማሰራት መርዳት አለባቸው:: ተማሪዎች ደግሞ በእውቀት፣በስነ ምግባርና ሌሎች ክህሎቶች ተገንብተው እንዲያድጉ ወላጆቻቸው፣መምህራንና ት/ቤቱ እያደረጉት ያለውን ርብርብ ዋጋ ሰጥተው ትምህርታቸውን በአግባቡ በመከታተል ወደፊት ለአገርና ለወገናቸው ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ አልመው መማር እንዳለባቸው መልዕክት በማስተላለፍ ነው::

የግል ትምህርት ቤቶች ምንም እንኳን ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበትና ስራቸውን የሚመሩበት መዋቅርና አመራር ቢኖራቸውም ተጠሪነታቸው ለመንግስት ትምህርት ተቋም ነው:: ከዚህ አኳያ በዚህ ጹሁፍ ለግል ት/ቤቶች ማሳያ ይሆናል ተብሎ የተመረጠው ወ/ሮ አየለች ደገፉ መታሰቢያ ት/ቤት ተጠሪነቱ ለባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ነው:: በዚህ የሁለቱ ተቋማት ግንኙነት መነሻነት የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ በስሩ ከሚገኙ 121 የግል ትምህርት ቤቶች ጋር በምን በምን ጉዳዮች ላይ አብሮ እንደሚሰራ፣ ት/ቤቶችን ስለሚደግፍበትና ስለሚከታተልበት አሰራር፣ ክፍተቶች ሲኖሩ ስለሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ሌሎች ጉዳዮች መረጃ የሰጡን ደግሞ በትምህርት መምሪያው ውስጥ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ባለሙያ የሆኑት አቶ ደረጀ እስከዚያ ናቸው::

ባለሙያው ከላይ በቀረበው ጽሁፍ ውስጥ ስለ ዘንድሮው ትምህርት ቅድመ ዝግጅትና አጀማመር፤ ስለክፍያ ጭማሪ አፈጻጸምና አወሳሰን ሂደት፣ስለወላጆች ተሳትፎና ትምህርት ጥራት ከወ/ሮ አየለች ደገፉ መታሰቢ ት/ቤት አንጻር በቀረበው መረጃ ላይ እንደሚስማሙ፣ ሌሎች አቻ የግል ትምህርት ቤቶችም የሚፈጽሟቸው ተግባራት እንደሆኑና ትምህርት

መምሪያውም ከግል ት/ቤቶች ጋር እየተገናኘ በጋራ የሚሰራቸው መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ በተለይ ክፍያ ጭማሪ በወላጆችንና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል አለመግባባት እየፈጠረ በትምህርት ስራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር ትምህርት መምሪያውንም እየፈተነ ያለ ጉዳይ መሆኑን ገልጸውልናል፡፡

የግል ት/ቤቶች ክፍያ የሚጨምሩ ከሆነ የአመቱን ትምህርት ከመዘጋታቸው ሁለት ወር ቀደም ብለው ግንቦት ወር ላይ በዕቅድ አስደግፈው ለትምህርት መምሪያው ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡ የመምሪያው ማኔጅመንት ኮሚቴም የክፍያ ጭማሪ እቅዱን ካሉት ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር አገናዝቦና በጥልቀት ገምግሞ የተጋነነውን የክፍያ ጭማሪ ቀንሶ፣ ተገቢ ነው ያለውንም አጽድቆ ለዕቅድ አቅራቢው የግል ት/ቤቶች ያሳውቃል፡፡ ለምሳሌ በዚህ አመት 50 ብር እና 100 ብር ብቻ ክፍያ ጭማሪ እንዲያደርጉ ትምህርት መምሪያው የወሰነባቸው የግል ት/ቤቶች እንዳሉና ውሳኔው አነሰ በሚል ጭማሪውን መተዋቸውን ነግረውናል፡፡ ይህን ውሳኔ ባለመቀበል በራሳቸው አሰራር ጭማሪ አድርገው ከወላጆች ጋር አለመግባባት ቢፈጠር ትምህርት መምሪያው ለማስማማት ጣልቃ በመግባት ወላጆችና የግል ትምህርት ቤቶች እስከ ሁለት ዙር ድረስ ስብሰባ አካሂደው አለመግባባቱን እንዲፈቱ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

ክፍያ ጭማሪን በሚመለከት አቶ ደረጀ አጽንኦት ሰጥተው የተናገሩት ለባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ፈታኝና ወደፊት በጥናት የታገዘ መፍትሄ ሊበጅለት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩ በሌሎች የመማር ማስተማር ተግባራት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ የጐላ ስለሚሆን የላላ አመራርና ኢንስፔክሽን እንዲኖር በር ከፍቷል፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት ያነሱት ጉዳይ የግል ትምህርት ቤቶችን ብዛትና የሚመጥን የኢንስፔክሽን ባለሙያ ስምሪት የሌለ መሆኑን ነው፡፡ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አንድ የግል ት/ቤት በሶስት አመት አንድ ጊዜ ብቻ የኢንስፔክሽን አገልግሎት እንደሚያገኝ ነግረውናል፡፡ ከዚህ አንጻር የግል ት/ቤቶች ከክፍያ ጭማሪ ጋር ተያይዞም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ቶሎ ቶሎ ኢንስፔክሽን እያገኙ ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸውን እየተከታተሉ በማስተካከል በኩል መምሪያው ላይ ክፍተት ስላለ በዚህ ዙሪያ ወደፊት ብዙ መሰራት እንደሚገባውም ተናግረዋል፡፡

አቶ ደረጀ አስተያየት የሰጡበት ሌላውና ዋናው ጉዳይ የትምህርት ስራው ነው፡፡ ትምህርት ለማስተማር በሁለንተናዊ መልኩ ደረጃውን የጠበቀ ት/ቤት ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጅ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እንደ ንግድ ሸቀጥ በተራ መጋዘን እና አስቀያሚ በሆነ ግቢ ውስጥ እንደነገሩ በሆነ መንገድ ትምህርት በማስተማር ርካሽ ትርፍ ማግበስበስን አልመው ት/ቤት የሚከፍቱ ባለሀብቶች አሉ፡፡ ትምህርት መምሪያው ይህን የተሳሳተ አስተሳሰብ ለማስተካከል ሁለት ስልት ይከተላል፡፡ አንደኛው በትምህርት ዘርፉ ላይ የተሰማሩትን ሁሉንም ባለቤቶች በመሰብሰብ ሰፊ ውይይቶችን ያደርጋል፡፡ ሁለተኛውና ዋናው ስልት ተከታታይነት ያለው ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ (ኢንስፔክሽን) ማካሄድ ነው፡፡ በሚደረገው ኢንስፔክሽን መንግስት ያስቀመጠውን ስርዓት ትምህርት አክብረው እያስተማሩ መሆኑን፣ለመማር ማስተማሩ ስራ አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሀይል፣ ልዩ ልዩ ግብዓች፣ ምቹ የሆነ የትምህርት አካባቢና ሌሎችም አይቀሬ ነገሮችን በመመልከት በተሳሳተ መንገድ የሚፈጸሙ አሰራሮችን እንዲያስተካክሉ እና ያላሟሉትን እንዲያሟሉ አስተያየት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ የማይስተካከሉ ከሆነ ትምህርት መምሪያው ማስጠንቀቂያ በመስጠት አለፍ ሲልም እውቅናቸውን በማንሳት ት/ቤቱን እስከመዝጋት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡ እስካሁን በተደረገው ኢንስፔክሽን ስራ በርካታ የግል ትምህርት ቤቶች ጉድለቶቻቸውን አሟልተው ለሌሎች አቻ የግል ትምህርት ቤቶች ተምሳሌት መሆን ችለዋል፡፡ ወደ ኋላ የቀሩትንም ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የግል ትምህርት ቤቶች ከትምህርት መምሪያው ጋር በቀጥታ ከሚያደርጉት ግንኙነት በተጨማሪ ጉዳያቸውን በተደራጀ መልኩ ጠቅለል አድርጐ ለትምህርት መምሪያውና ለሌሎችም የመንግስት ትምህርት ተቋማት የሚያቀርቡበት ማህበር አላቸው፡፡ ማህበሩ የራሳቸውን ውስጣዊ ጉዳዩች በጋራ እንዲወያዩ በማመቻቸት የትምህርት አሰጣጥ ሂደታቸውን በመገምገምና በመደጋገፍ ወጥ የሆነ የትምህርት አሰጣጥ እንዲኖር የራሳቸውን ኢንስፔክሽን እንዲያደርጉም ይረዳቸዋል፡፡

በመጨረሻም የግል ት/ቤቶች ትምህርት ትውልድ (ሰው) የሚገነባበት ዋነኛ መሳሪያ መሆኑን ተገንዝበው የገቡትን ቃል አክብረው በትልቅ ሀላፊነትና ተቆርቋሪነት ሊሰሩ ይገባቸዋል፡፡ ርካሽ ትርፍን ወይም ገንዘብን ብቻ በማሰብ ትውልድንና አገርን ከመጉዳት ይቅርብኝ ብሎ ስራውን ትቶ መውጣት በጥሩ ተቆርቋሪነት፣ ባለውለታነትና አርቆ አሳቢነት ስለሚወሰድ የመልካም ዜጋ ባህሪ ነው የሚል መልዕክት በማስተላለፍ ገለጻቸውን ቋጭተዋል፡፡

እኛም መረጃ በመስጠት የተበበሩንን ግለሰቦችና ተቋማት እያመሰገን የግል ትምህርት ቤቶች የሚጨምሩትን ክፍያ ከወላጆች ጋር ግልጽ ውይይት በማካሄድ አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ ጭማሪ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ኃላፊነት እንዳለባቸውም አውቀው ትውልድ ለመገንባት የዜግነት ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን ሳይዘነጉ መስራት ይገባቸዋል እንላለን- ሰላም፡፡

# ከእረኝነት ባሻገር

በደፋሩ እምሬ

“ችግር ብልሀትን ይፈጥራል” እንዲሉ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ላጋጠሙት ውጣ ውረዶች መላ እየዘየደ ኑሮውን ቀላልና የተሳካ ለማድረግ ይለፋል፤ይደክማል፡፡ የሚፈጥረው “ብልሀት” ከሀሳብ አልፎ ወደ አንዳች ተጨባጭ ቁስ(እቃ) ተለውጦ ፈጠራ ውጤት ሆኖ ብቅ ይላል፡፡ በዚህ አይነት ሂደት ውስጥ አልፈው አለምን አጃይብ ያስባሉ የፈጠራ ሰዎችና የፈጠራ ውጤቶች ብዙ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያም ነባራዊ ችግሮችን መነሻ ያደረጉ የፈጠራ ቴክኖሎጅዎች የፈጠራ ችሎታ ባላቸው ዜጎች ተሰርተው ታይተዋል፡፡ መንግስትም ይህን ጉዳይ አልፎ አልፎ የፈጠራ ችሎታ መወዳደሪያ መድረኮችን እያዘጋጀ ፈጣሪዎችን ለማበረታታት ሲሞክር ይስተዋላል፡፡

በአማራ ክልልም የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ዜጎች ስራዎቻቸውን ይዘው በሚዲያም ይሁን ፊት ለፊት ብቅ እያሉ ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡ የፈጠራ ስራዎቻቸውም ተጠቃሚዎች ጋ ደርሰው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ አሉ፡፡ ውድ አንባቢዎቻችን እኛም በክልሉ ካሉት የፈጠራ ባለቤቶች መካከል ለዛሬ የአንዱን ግለሰብ የፈጠራ ታሪክ ጉዞ እናስቃኛችኋለን፡፡ መልካም ንባብ፡፡

አቶ ባንታለም አዩ ይባላል፡፡ በ30ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ቀልጣፋ፣ ታታሪና ትሁት ወጣት ነው፡፡ ተወልዶ ያደገው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ጐጃም ዞን ደጀን ከተማ ዙሪያ በሚገኝ ጢቅ በሚባል ቀበሌ ነው፡፡ ለወላጆቹ ሰባተኛና የመጨረሻ ልጅ ነው፡፡ ወላጆቹ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡

አቶ ባንታለም የቁሳዊ ፈጠራ ቴክኖሎጅዎች ባለቤት ነው፡፡ በደብረ ማርቆስ ከተማ “ባንታለም አዩ አጠቃላይ የብረታ ብረት ስራ ድርጅት” አቋቋሞ በባለቤትነትና በስራ አስኪጅነት ይመራል፡፡

የአቶ ባንታለም አዩ የህይወት ታሪክ ጉዞ እንደመጀመሪያ ምዕራፍ ሊወሰድ የሚችለው በእረኝነት ያሳለፈው ጊዜ ነው፡፡ ከአራት አመቱ ጀምሮ እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ከከብቶች ጋር ውሎ እየገባ የእረኝነት ስራውን ተያያዘው፡፡ ይሁን እንጅ የባንታለም የእረኝነት ጊዜ ብዙም ሳይቆይ የሚያከትምበት ወሳኝ ክስተት ተፈጠረ፡፡ ወላጆቹ ወደደጀን ከተማ ገብተው ለመኖር ወሰኑ፡፡ 1987 ዓ.ም ላይ ባንታለም አዩ ከብቶቹንና እረኝነቱን ገጠር ትቷቸው ከወላጆቹ ጋር ደጀን ከተማ ላይ ከተመ፡፡

አዲስ አካባቢ፣ አዲስ የስራ ድርሻ፣አዲስ አስተሳሰብ መጣ፡፡ ባንታለም ወደ ትምህርት ቤት ይግባ ተብሎ ተወሰነ፡፡ በመሆኑም በደጀን ከተማ 02 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንደኛ ክፍል ገባና ሁለተኛው የህይወት ታሪኩ ጉዞ በመማር ተጀመረ፡፡  ልጁ የዋዛ አልነበረምና የአንደኛ ክፍል ፊደል ቆጠራውን በቶሎ አቀላጥፎ አጠናቀቀ፡፡ በስነ-ስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ችሎታውም ጉበዝ እየሆነ መምጣቱ ከትምህርት ቤቱ አልፎ ቤተሰቦቹ ጆሮ ደረሰ፡፡ ይህንን የሰሙት አባቴ ጊዜዬን በዋዛ ፈዛዛ ሳላባክን ለቀለም ትምህርቶች ትኩረት ሰጥቼ እንዳጠና አዘውትሮ ይመክረኝ ነበር ብሏል፡፡ የክፍል ደረጃው እየጨመረ ሲሄድ የስነ-ስዕልና ቅርጻ ቅርጽ ችሎታው ብቻ እየጨመረ በቀለም ትምህርቶች አቀባበል ግን እየቀነሰ መሄዱንም አጫውቶናል፡፡

አቶ ባንታለም ገጠር ከብት እረኛ በነበረበት ወቅት ጭቃ አቡክቶ መኪና፣ቤት፣ እንስሳት፣ ሰው፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን በቅርጻ ቅርጽ ይሰራ ነበር፡፡ ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ ደግሞ ስዕል የመሳል ችሎታውን አዳብሮ ሰዎችን አስመስሎ መሳል ያዘወትራል፡፡ የወዳደቁ ሸቦዎችን፣ ካርቶንና ሌሎችንም ቁሳቁሶች በመሰብሰብም መኪና፣ አውሮፕላን፣ ጠመንጃ፣ወዘተ. የመስራት ፈጠራ ችሎታም እንደነበረው ያስታውሳል፡፡

የመካኒካልና ቴክኒካል ፍላጐት እንዲያድርበትና ወደዚያ የመሳብ ዝንባሌው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገው ደግሞ በናፍጣ ይሰራ የነበረው የአባቱ የእህል ወፍጮ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ከአባቱ ጋር አልፎ አልፎ ወደ ወፍጮው እየሄደ እንዴት እንደሚሰራ፣ እያንዳንዱን የወፍጮውን ክፍሎች እየተመለከተ ይገረማል፤ይመራመራል፡፡ በተለይ ወፍጮው ብልሽት አጋጥሞት ከሌላ ቦታ ለመጠገን የሚመጡት መካኒኮች ፈታተው የተበላሸውን አስተካክለው መልሰው ሲገጣጥሙት ሲመለከት ምነው እኔም እንደነሱ በቻልኩ እያለም ይመኛል፡፡ መካኒኮቹ መጥተው ወፍጮውን ፈታተው ሲሰሩ ለመመልከት ወፍጮው ቶሎ ቶሎ እንዲበላሽ እንደሚፈልግም ነግሮናል፡፡ እንደፈለገውም ባይሆን ወፍጮው አልፎ አልፎ በሚያጋጥመው ብልሽት  ሳቢያ ባንታለም ከመካኒኮች ጋር ተጠግቶ መፍቻ የማቀበል፣የሚፈታቱ ብሎኖችን የመሰብሰብ፣ የመንካትና መልሶ የመገጣጠም መለማመጃ እድል እንዲያገኝ በር ከፍቶለታል፡፡ ቀስ በቀስ የመካኒኮችን ያክል እንኳ ባይሆንም ብልሽቱን የመለየትና ያለቦታቸው የተገጠሙ ብሎኖችንና አካላትን ለመካኒኮች መናገርና ማሳየት በመጀመሩ “ህጻኑ ረዳት ሜካኒክ” የሚል ስም አወጡልኝ ብሏል፡፡ በዚህ ስም በመጠራቱ በጣም ደስ እንዳለውና ወደፊት መካኒክ የመሆን ፍላጐቱን እንደጨመረለት አጫውቶናል፡፡

ባንታለም ይህን ያደርግ የነበረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እየተማረ በነበረበት ወቅት በመሆኑ ወደወፍጮው መመላለስ ማዘውተሩን



የተለያዩ

”ወጣቶች ሰርቼ እለወጣለሁ፤ ያሰብኩት ስኬት ላይ እደርሳለሁ፤ የሚል አቋም፣ራዕይና አላማ ሊኖራቸው ይገባል”

አቶ ባንታለም አዩ በስራ ላይ

የተመለከቱት አባቱ እንዳይሄድ ገስፀው እንደከለከሉትና ትምህርቱን ትኩረት ሰጥቶ እንዲከታተል በተደጋጋሚ ይመክሩትም ነበር:: በእንዲህ አይነት ክንውኖች ታጅቦ ሲጓዝ የነበረው የደጀን ከተማ 02 አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የባንታለም ትምህርት ታሪክ 1992 ዓ.ም ላይ የ8ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስዶ 49 በመቶ የሆነ ዝቅተኛ ውጤት አምጥቶ ተቋጨ::

የስምንተኛ ክፍል ውጤቱ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተዛውሮ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዲቀጥል የሚያስችለው ሆኖ በመገኘቱ ለመማር ተዘጋጀ:: ይህ የሚሆነው ግን ደጀን ከተማ ላይ ሳይሆን አዲስ አበባ እንደሚሆን ወላጆቹ መከረው ወሰኑ:: ታላቅ እህቱ አዲስ አበባ ስለምትኖር ከእሷ ጋር ሆኖ ለመማር ጓዙን ጠቅልሎ አዲስ አበባ ገባ::

አዲስ አበባ ላይ የቀጠለው የባንታለም የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ታሪክ ከቀን ወደ ማታ ፕሮግራም ተቀየረ:: በማታው ፕሮግራም እየተማረ ቀን ስራዎችን እየሰራ ገንዘብ ማግኘት ጀመረ:: በዚህ መልኩ ዘጠነኛንና 10ኛ ክፍሎችን አጠናቀቀ:: የ10ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተናን ወስዶ ሁለት ነጥብ ሁለት አመጣ:: ውጤቱ በወቅቱ ወደ መሰናዶ የሚያስገባው ቢሆንም ቴክኒክና ሙያ ት/ቤት ገብቶ ቶሎ ስራ ማግኘት እንዳለበት ወስኖ አዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመሰልጠን ወሰነ:: በተግባረ እድ ት/ቤትም ጀነራል መካኒክስ ስልጠና ዘርፍን መርጦ ቀጠለ:: በዚህ የስልጠና ዘርፍ እንደ “መሰረታዊ ስራ” ያሉ ኮርሶችን በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ወስዷል:: ይህን ኮርስ ሰልጥኖ እንደጨረሰ ተግባራዊ ልምምድ የጀመረው በአጼ ሀይለስላሴ ዘመን ተገዝተው ያለስራ የተቀመጡ ትላልቅ ማሽኖችን በማንቀሳቀስ ነበር:: ማሽኖቹ በዘይትና በናፍጣ የሚሰሩ የአሉሚኒየምና ነሀስ ማቅለጫዎች ናቸው:: እነዚህን ማሽኖች ሲነካካና ሲያንቀሳቀስ የአባቱ እህል ወፍጮ ትዝታ ድቅን ይልበት እንደነበር ነገሮናል::

ባንታለም እነዚህን የተግባረ ዕድ ማሽኖች በማንቀሳቀስና የሚጠገኑትንም ጠግኖ አገልግሎት እንዲሰጡ በማዘጋጀቱ ት/ቤቱ እውቅና እንዲያገኝ ከማድረግ በተጨማሪ የራሱን የመካኒክነት ችሎታ ያሳየበትና ያዳበረበት እንደነበር ያስታውሳል:: ከስልጠናው ጐን ለጐንም በደጀን ከተማ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ህይወቱ አብሮት ያደገውን ስዕል የመሳልና ቅርጻ ቅርጾችን የመቅረጽ ፍላጐቱንና ዝንባሌውን በተግባረ እድ ት/ቤትም በማስቀጠል ጥሩ ጊዜን አሳልፏል::

ተግባረ ዕድ ት/ቤት ወደ ኮሌጅ ደረጃ አድጐ “ተግባረ ዕድ ኮሌጅ” ሲባል የስያሜውን አማርኛ ፊደሎች በትልቁ በብረት የቀረፀው እሱ መሆኑን ይናገራል:: በተግባረ ዕድ ኮሌጅ ቆይታው ከመደበኛ ስልጠና ባሻገር በትርፍ ጊዜው በኮሌጁ ክበባት ውስጥ በሚከናወኑ ጥገናዎች ላይ በመሳተፍ ጠቀም ያለ ገንዘብ ያገኝ ነበር:: በዚህ መልኩ በተግባረ ዕድ ኮሌጅ ስልጠናውን ሲያካሂድ ቆይቶ በ1997 ዓ.ም በጀነራል መካኒክስ በዲፕሎማ ተመረቀ:: ተግባረ ዕድ ኮሌጅ መካኒክ የመሆን የልጅነት ፍላጐቱን እውን ያደረገለት፣ቴክኒካል የፈጠራ ዝንባሌውን አውጥቶ የተለማመደበት፤ወደፊት እንዲኖረው የሚፈልገውን የራሱን የብረታ ብረት ጋራዥና በዚያ ውስጥ እንደፈለገ ሊተገብረው የሚመኘውን የፈጠራ ስራውን እውን እንዲያደርግ ስንቅ የሰጠው፤መነሻ ሀሳብ ያገኘበትና አቅጣጫ ያየበት መሆኑን አጥብቆ ይመሰክራል::

ከተግባረ ዕድ ኮሌጅ ምረቃ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የከርሰ ምድር ውሃ የሚቆፍር ድርጅት ውስጥ በረዳት ማሽን ኦፕሬተርነት ተቀጠረ:: ማሽኑን እንዴት እንደሚያንቀሳቅስ እየተለማመደ ሶስት ወራት ያክል ከሰራ በኋላ የሚከፈለው ደመወዝ አነስተኛ መሆንና ረዳት ኦፕሬተር ሆኖ መስራት ስላልተመቸው ለቆ ወጣ:: ወዲያውኑ አንድ የሸራ ፋብሪካ ውስጥ ሙሉ ኦፕሬተር ሆኖ ተቀጥሮ ከነጮች ጋር በመሆን አዲስ አበባ ዱከም አካባቢ ሙሉ

ፋብሪካ ተከላ ላይ ተሳትፏል፡፡ በሸራ ፋብሪካው ውስጥ በነበረው ቆይታ የሚበላሹ ማሽኖችን በመጠገን፤ አዳዲስ ማሽኖችን በመፍጠርና መለዋወጫ እቃዎችን በመቅረጽ የመካኒካል፣ቴክኒካልና ፈጠራ ችሎታውን እንዳዳበረ አጫውቶናል፡፡ ፋብሪካውም አዳዲስ ማሽኖችንና መለዋወጫ እቃዎችን ከውጭ ለማስገባት ያወጣው የነበረውን ከፍተኛ ወጭ እንዲያስቀር የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ የሙያ ግዴታውን እንደተወጣ ተናግሯል፡፡ ባንታለም ፋብሪካው ከሚከፍለው ደመወዝ ላይ እየቆጠበ ወደፊት የግሉን ጋራዥ በመክፈት የፈጠራ ፍላጐቱን የማሳካት ራዕይ ስለነበረው ለዚያ የሚሆን የገንዘብ አቅም መፍጠር ችሎ ነበር፡፡

በሰለጠነበት የመካኒክነት ሙያ የሚመራው የእኔ የሚለው የብረታ ብረት ጋራዥ ራዕዩን 2000 ዓ.ም ላይ እውን ለማድረግ ወሰነ፡፡ ይሰራበት የነበረውን ሸራ ፋብሪካ በራሱ ፈቃድ ለቀቀ፡፡ ስራውን የሚጀምረው ከአዲስ አበባ ውጭ መሆን እንዳለበትም ራሱን አሳመነ፡፡ ምክንያት አድርጐ የወሰደው ደግሞ ያለው የገንዘብ አቅም ወደ ክፍለ ሀገር ወጣ ብሎ የሚያሰራ እንጅ አዲስ አበባ ላይ መስሪያ ቦታ ተከራይቶ፣ መሳሪያዎችን ገዝቶ መስራት እንደማይችል ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ከአዲስ አበባ ወጥቶ ለመስራት የመጀመሪያ ምርጫው ያደረገው ምስራቅ ጎጃምን ነው፡፡ እናም ሳይውል ሳያድር ሸገርን ተሰናብቶ ጓዙን ጠቅልሎ መንቆረር(የደብረ ማርቆስ ከተማ የድሮ ስም) ላይ ከተመ፡፡

ደብረ ማርቆስ ላይ እቅዶቹ ሁሉ በጥሩ ሁኔታ እንደሄዱለት ያስታውሳል፡፡ በተመጣጣኝ ኪራይ መስሪያ ቦታ አገኘ፤ መኖሪያ ቤትም እንዲሁ አቅሙን በመጠነ ዋጋ ተከራየ፡፡ የብረታ ብረት ስራውንም የመበየጃ ማሽኖችንና ግራይንደሮችን ራሱ አዘጋጅቶ የጋራዥ ስራውን አሀዱ አለ፡፡ ደንበኞችን እያፈራና ስራው እየታወቀ በመሄዱ 2003/2004 ዓ.ም ላይ የኮንክሪት ማውጫ ማሽኖችን ትላልቅ የህንጻ ግንባታ ከሚያከናውኑ ባለሀብቶችና ድርጅቶች ጋር በመዋዋል ስራውን ማቀላጠፍ ተያያዘው፡፡

ከደብረ ማርቆስ ከተማ ነባራዊ ችግሮች በመነሳትና ከሰዎች በሚቀርቡለት የስራልን ጥያቄ መሰረት በገጠርም ይሁን በከተማ የህብረተሰቡን ድካም የሚቀንሱ፣ጊዜን የሚቆጥቡ፣ኑሮንና አሰራርን የሚያዘምኑና የሚያቀላጥፍ ቁሳዊ የፈጠራ ማሽኖች ላይ ትኩረት አድርጐ ይሰራል፡፡ በእንጨት የሚሰራ ተንቀሳቃሽ የዳቦ መጋገሪያ በመፍጠር ለዳቦ ጋጋሪዎች በማቅረብ በገጠርም ሆነ በከተማ ዳቦ መጋገርና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን አስችሏል፡፡ በገጠር ለአርሶ አደሩ ቀኝ እጅ የሆኑ የበቆሎ መፈልፈያ፣የጤፍና የስንዴ መውቂያ፣በጀኔረተር የሚሰራ የበቆሎ መኮትኮቻ፣የአረቂ ማውጫ፣የክክ መከኪያና ሌሎችንም ቁሳዊ የፈጠራ ማሽኖችን ህዝቡ በግሉና በቡድን እየገዛም ሆነ እየተከራየ አገልግሎት እያገኘ ነው፡፡ ከእነዚህ ማሽኖች ብዙዎችን በአካል ተገኝተን በጋራዥ ውስጥ ተመልክተናቸዋል፡፡ በቀጣይም የአካባቢውን ህብረተሰብ ፍላጎትና ነባራዊ ችግሮች መነሻ በማድረግ ቁሳዊ የፈጠራ ማሽኖችን በመስራት ህዝቡንም ራሱንም ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት ማድረጉን ቀጥሏል፡፡

የባንታለም ቁሳዊ የፈጠራ ቴክኖሎጅ ማሽኖች የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተፈጠሩ በመሆናቸው ከውጭ ከሚገቡት ተመራጭ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለማንቀሳቀስ ምቹ የሆኑ፣ክብደታቸው ቀላል፣ ዋጋቸው ተመጣጣኝ፣ በየትኛውም አካባቢ በሰው ጉልበት ሁሉ መጓጓዝ ይችላሉ፡፡ ጥንካሬቸው፣ በስራ ላይ ፍጥነታቸው፣ጊዜ ቆጣቢያነታቸውና በቀላሉ መጠገን መቻላቸው በብዙ ተጠቃሚዎች ዘንድ ተመራጭ የሆኑ ቁሳዊ የፈጠራ ቴክኖሎጅዎች መሆናቸውን ተናግሯል ፡፡

"ባንታለም አዩ ጠቅላላ የብረታ ብረት ስራ ድርጅት" በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለብዙ ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል፡፡ በቋሚነት ሶስት የብየዳና መካኒክ ባለሙያዎች በድርጅቱ ውስጥ ይሰራሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ሰፊ የስራ እድል የተፈጠረው ማሽኖችን ገዝተው ወይም በኪራይ ወስደው በሚያሰሩት ግለሰቦች፣ባለሀብቶችና ድርጅቶች አካባቢ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የበቆሎ መፈልፈያ ወይም ጤፍ መውቂያ ማሽን ወስዶ የሚያሰራ አካል ማሽኖችን ለሚያንቀሳቅሱት፣ በቆሎ ለማሽኑ ለሚያቀርቡ፣የተፈለፈለውን ምርት ለሚሰበስቡት፣ በማጥራት፣ በኩንታል በመከዘንና በማጓጓዝ ለሚሳተፉት በርካታ ዜጐች ሁሉ የስራ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

በዚህ መልኩ የቀጠለው የባንታለም አዩ የፈጠራ ማሽኖችን ለስራ ዕድል ፈጠራ የመጠቀም በጐ ተግባር በክልልና በፌደራል ደረጃ እውቅና አግኝተዋል፡፡ በ2013 ዓ.ም ደሴ ላይ ፈጠራ ቴክኖሎጂ ማሽኖች ውድድር ነበር፡፡ ለውድድሩ የበቆሎ መፈልፈያና የስንዴ መውቂያ ማሽኖች ቀርበው ሁለተኛና ሶስተኛ ወጥተው በክልልና በፌደራል ደረጃ የእውቅና የምስክር ወረቀት ተሸልሟል፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም የፈጠራ ማሽኖች እንደ ክልልም ሆነ አገር ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት የባንታለም ድርጅት ጥረት እያደረገ ነው፡፡ መንግስት የሚያዘጋቸው የውድድር መድረክ ለዚህ ተግባር ሚናው የጐላ ቢሆንም ድርጅቱ የበኩሉን የማስተዋወቅና የማስፋፋት ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህ አንፃር ደቡብ ክልል ድረስ የበቆሎ፣የጤፍና የስንዴ መውቂያ ማሽኖች እየተላኩ አገራዊ ተደራሽነታቸውን ለማስፋፋት ጥረት እየተደረገ ነው ብሏል፡፡ በተለይ በአማራ፣በደቡብና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ውስጥ ሰፋፊ የበቆሎ፣ የጤፍና የስንዴ እርሻ ያላቸው ባላሀብቶች የፈጠራ ማሽኖችን በግዥና በኪራይ እየወሰዱ በማስተዋወቅና በማስፋፋት በኩል ሚናቸው የላቀ እንደሆነ ገልጾልናል፡፡

በዚህ ሁሉ ጥረት መካከል ያገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት በሚመለከትም ባንታለም አጫውቶናል፡፡ ከኢኮኖሚ አንፃር ዘመናዊ መኖሪያ ቤት እንደሰራ፣ ለስራም ይሁን ለቤተሰብ ማጓጓዣ




ከአቶ ባንታለም ፈጠራ ውጤቶች በከፊል

የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች እንዳሉት፣በርከት ያለ ተቀማጭና ተንቀሳቃሽ ሀብትም አለው፡፡ ከማህበራዊ ተጠቃሚነት ጋር በተያያዘም በርካታ ደንበኞች አፍርቷል፤ታዋቂነቱም አድጓል፡፡ የፈጠራ ማሽኖቹን የሚፈልጉና የሚጠቀሙ የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎች፣በዙሪያው ያሉ አርሶ አደሮች ፣ባለሀብቶችና ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነትና ማህበራዊ ትስስር ፈጥሯል፡፡ ቤተሰብም መሰርቶ የሁለት ልጆች አባት ሆኗል፡፡

ከእርኝነት እስከ ፈጠራ ባለቤትነት በተደረገው የባንታለም የህይወት ጉዞ ቤተሰቦቹ፣ መምህሮቹ፣ ጓደኞቹ፣ ተቀጥሮ ይሰራባቸው የነበሩ ድርጅቶች፣የተማረባቸው ት/ቤቶችና ኮሌጆች፣ የደብረ ማርቆስ ከተማ ህዝብ፣ ባለሀብቶችና ግለሰቦች ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ድጋፍ አድርገውልኝ እዚህ ደረጃ ላይ ስላደረሱትም አመስግኗል፡፡ መንግስትም ቢሆን በፈጠራ ውድድር መድረኮች ላይ በመሳተፍ የልምድ ልውውጥ እንዳደርግና የፈጠራ ስራዎቼን የማስተዋወቅ እድል ፈጥሮልኛል፡፡ የመንግስት ተቋም የሆነው ደብረ ማርቆስ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ትላልቅ ማሽኖች ስላሉት ለፈጠራ ስራዎች የሚሆኑ አንዳንድ ቅርጻ ቅርጾችን ለማዘጋጀት ስጠይቅ በደስታ ተቀብሎ በማስተናገድ በእጅጉ እየተባበረኝ ነው ብሏል፡፡

“የሚፈለገውን ያላገኘ ልብ ሁሌም መንገደኛ ነው” የሚለው አባባል ከባንታለም የህይወት ትንቅንቅ ጋር በቀጥታ ይያያዛል፡፡ የሚፈልጉትን ለማግኘት ጥሩ ወይም መጥፎ አጋጣሚዎችን ማለፍ ግድ ይላል፡፡ ከዚህ አንፃር ባንታለም እዚህ ለመድረስ በርካታ ጥሩ አጋጣሚዎችን አግኝቷል፡፡ ቤተሰቦቹ ከገጠር ወደ ከተማ መግባታቸውና ትምህርት የመማር እድል ማግኘቱ መልካም አጋጣሚ ነው፡፡ የአባቱ ወፍጮ መኖሩ ቴክኒካልና መካኒካል ፍላጎት አድሮበት ዛሬ ላይ ለደረሰበት ስኬት መሰረት እንደሆነው ያስታውሳል፡፡ ሌላው ጥሩ አጋጣሚ ተግበረ ዕድ ኮሌጅ ገብቶ በጀነራል መካኒክስ የመሰልጠን እድል ማግኘቱ ነበር፡፡ ከዚያም ስራ ተቀጥሮ የሰራባቸው ድርጅቶች፣ፋብሪካዎች ሁሉ በጥሩ አጋጣሚነት የሚወሰዱ ናቸው ብሏል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ መጥፎ አጋጣሚዎችም መከሰታቸው ተፈጥሮዊ ባህሪ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አቶ ባንታለም ፍላጎቱን፣ዝንባሌውን በፈለገው ልክ ተግባራዊ እንዳያደርግ መሰናክል የነበሩት የገንዘብ እጥረት፣አልፎ አልፎ በፈጠራ ማሽኖች ላይ የሚከሰተው ብልሽትና ሊያደርሱበት የነበረውን ጉዳት እንደ መጥፎ አጋጣሚ ይወስደዋል፡፡ በስራ ላይ ህይወቱን የሚያሳጣ አደጋም አጋጥሞት ከሞት የተረፈበት መጥፎ አጋጣሚ እንደነበርም ነግሮናል፡፡

በመጨረሻም የልጅነት ህልማቸውን ማሳካት ለሚፈልጉ፤ የፈጠራና ሌሎች ፍላጎቶቻቸውን፣ ዝንባሌያቸውን እውን ማድረግ ለሚያልሙና ራዕይ ላላቸው ዜጐች ሁሉ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፏል፡፡ “ጠባቂነት ትልቁ የለውጥ መሰናክል በመሆኑ ዜጐች ከዚህ እኩይ አስተሳሰብ መላቀቅ አለባቸው፡፡ ከዚህ ይልቅ በራስ ሰርቶ ማግኘትና ማደግ ተመራጭም አዋጭም እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተሰጠው ክህሎት ስላለ ያንን አውቆ ስራ ላይ በማዋል ሰርቶ ራስን ማሻሻል እንደሚቻል ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ዜጐች የራሳቸው የስራ እምነት ኖሯቸው እለወጣለሁ፤ ያሰብኩት ቦታ ላይ እደርሳለሁ የሚል አቋም፣ራዕይና አላማ ይዘው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል ብሏል፡፡”

እኛም አቶ ባንታለም ከገጠር እረኝነት እስከ ፈጠራ ባለቤትነት የነበረውን ረጅም የህይወት ስኬትማ ጉዞ በተለይ ደግሞ ያጋጠመውን መሰናክሎች ሁሉ በጥሩ መሸጋገሪያ ድልድይነት ተጠቅሞባቸው በፅናት በማለፍ ለዛሬ ስኬቱ እንዴት እንደበቃ ለማሳየት ሞክረናል፡፡ የዚህ ሰው ተሞክሮም ከመንግስትና ከግል ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ተመርቀው ቁጭ ብለው ስራ ለሚጠብቁ፣ጊዜያቸውን በዋዛ ፈዛዛ ለሚያባክኑ በሺዎች ለሚቆጠሩ ወጣቶች በግልም ይሁን በቡድን ተደራጅተው የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ራሳቸውን፣ቤተሰባቸውንና አገራቸውን ለመጥቀም እንዲነሳሱ የሚያደርግ መሆኑን ያሳየንበትን ዝግጅት በዚህ ቋጨን ሰላም፡፡





በአማራ ክልል የሚገኙ ጥብቅ ስፍራዎች

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
AMHARA INNOVATION AND TECHNOLOGY BUREAU

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
AMHARA INNOVATION AND TECHNOLOGY BUREAU

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
AMHARA INNOVATION AND TECHNOLOGY BUREAU



ደቡብ ወሎ ዞን በቃሉ ወረዳ የቦርከና ወንዝ



ዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አሥተዳደር የዝቋላ እና ስሃላ ሰየምት ወረዳን የሚያገናኘው የተከዜ የብረት ድልድይ